# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

81ኛ ዓመት ቁጥር 210 መጋቢት 30ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!





# “የፐብሊክ ዲፕሎማሲው በአገሪቱ የተደቀነውን ዓለም አቀፍ ጫና ለመቋቋም ወሳኝ ነው”

-አምባሳደር ዲና ሙፍቲ
የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ



**ሞገስ ተስፋ**

ጎንደር:-የፐብሊክ ዲፕሎማሲው በአገሪቱ የተደቀነውን ዓለም አቀፍ ጫና ለመቋቋም ወሳኝ መሆኑን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አምባሳደር ዲና ሙፍቲ ገለጹ።

አምባሳደር ዲና በሳምንቱ ውስጥ በተከናወኑ አብይት አገራዊ የዲፕሎማሲ፣ የማህበራዊና ኢኮኖ ሚያዊ እንቅስቃሴዎች ዙሪያ ትናንት በጎንደር ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፣ የመደበኛው ዲፕሎማሲ ሥራ በፐብሊክ ዲፕሎማሲው መታገዙ ውጤታማ የዲፕሎማሲ ሥራ ለማከናወን ያስችላል።በመደበኛ የዲፕሎማሲ ሥራ ብቻ ውጤታማ ሥራ መስራት አይቻልም። ምክንያቱም የፐብሊክ ዲፕሎማሲው በአገሪቱ የተደቀነውን ዓለም አቀፍ ጫና ለመቋቋም ወሳኝ ነው፡፡

ፐብሊክ ዲፕሎማሲ መደበኛውን ዲፕሎማሲ የሚያግዝና የሚያጠናክር መሆኑን ገልጸው፤በመላው ዓለም የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅም ለማስከበር የቢዝነስ ተቋማት፣ የእምነት ተቋማት፣ ታዋቂ ግ ለሰቦችና እያንዳንዱ

“የፐብሊክ ዲፕሎማሲው... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




# ህወሓት በወልቃይት ጠገዴና ጠለምት ህዝብ ላይ የዘር ጭፍጨፋ መፈጸሙን በጥናት እንዳረጋገጠ የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ገለጸ

**ሞገስ ተስፋ**

ጎንደር:- ህወሓት ላለፉት 40 ዓመታት በወልቃይት ጠገዴና ጠለምት አካባቢዎችን በመውረር ጭቆና ማድረሱን፣ ሌላ ማንነት እንዲላበሱ ማድረጉን፣ በጅምላ በዋሻ በማሰር ስቃይ ማድረሱን፣ የዘር ጭፍጨፋ መፈጸሙን ባካሄደው ጥናት እንዳረጋገጠ የጎንደር ዩኒቨር ሲቲ አስታወቀ።

የጥናት ቡድኑ መሪ ረዳት ፕሮፌሰር ጌታ አስራደ የቡድኑን ጥናት አስመልክቶ በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፤ ህወሓት ላለፉት 40 ዓመታት በወልቃይት ጠገዴና ጠለምት አካባቢዎች በመዝለቅ ጭቆና አድርሷል፣ ማንነታቸውን በመግፈፍ ሌላ ማንነት እንዲላበሱ አድርጓል፣ በጅምላ በዋሻ በማሰር ስቃይ አድርሷል፣ ረሽኗል፡፡

እንደ ጥናት ቡድኑ ገለጻ፤ ህወሓት ከ1968 ዓ.ም ጀምሮ አማራ ታሪካዊ ጠላቴ ነው ብሎ ባዘጋጀው ማኒፌስቶ መሰረት በ1972 ዓ.ም ወደ አካባቢዎቹ በመዝለቅ የማንነት ጭቆና፣ ማንነታቸውን በመግፈፍ ሌላ ማንነት እንዲላበሱ ማድረጉን፣ በጅምላ በዋሻ በማሰር ስቃይ ማድረሱንና እንዲረሸኑ አድርጓል።

በተባበሩት መንግሥታት ህግጋት 1949 መሰረት ህወሓት የፈጸመው ጭፍጨፋ በዘር ፍጅት የሚያስጠይቀው ወንጀል መሆኑ ተመልክቷል። ጥቅል ጥናቱ ወደፊት የሚገለጽ ቢሆንም በተደረገው ጥናት 12 የሚሆኑት የጅምላ መቃብሮች መገኘታቸውን ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ እንዲገነዘብና በቦታው ተገኝቶ ምልከታ ሊያደርግ ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።



ፎቶ:ኢዮብ ተፈራ

የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ከተለያዩ የትምህርት ክፍሎች ባዋቀረው 21 የጥናት ቡድን በማይካድራ የተፈጸመውን የዘር ጭፍጨፋ መሰረት በማድረግ ለአንድ ዓመት ከሶስት ወር ህወሓት በወልቃይት ጠገዴና ጠለምት ህዝብ ላይ የፈጸመውን ሁለንተናዊ ጥቃትና ግፍ የተመለከተውን ጥናት ይፋ አድርጓል፡፡

ቡድኑ በአካባቢዎቹ የዘር ጭፍጨፋ መፈጸሙን በጥናት ማረጋገጥ መቻሉን የጠቆሙት ረዳት ፕሮፌሰር ጌታ አስራደ፤ ህወሓት በወልቃይት ጠገዴ የፈጸመው የጅምላ ፍጅት የጀርመኑ ናዚ በይሁዳውያን ላይ ከፈጸመው የዘር ማጥፋት ጋር ተመሳሳይነት አለው ብለዋል፡፡

በማህበረሰቡ ላይ ሰብዓዊ ጥሰት፣ ኢኮኖሚያዊ ጫና፣ ማፈናቀልና በጠለምትና በወልቃይት ጠገዴ ማህበረሰብ ላይ ስልታዊና ተቋማዊ በሆነ መንገድ የዘር ጭፍጨፋና ጅምላ ጭፍጨፋ ማድረሱን በጥናቱ መረጋገጡን ጠቅሰዋል።

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ የትግራይና የአማራ ህዝብ የውጭ ጠላታቸውን በአንድነት የታገሉ፣ የጋራ ባህልና የእምነት ፤አንድነት ያላቸው ህዝቦች መሆናቸው በጥናቱ ተለይቷል፡፡ ይሁን እንጂ ህወሓት ከተፈጠረ

ህወሓት በወልቃይት... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# ‹‹ወደ ትግራይ የገባው የሰብዓዊ እርዳታ ለተቸገረው ህዝብ በትክክል መድረስ አለበት››

-አቶ ገብረፃድቅ ገብረመድህን

**መኣረግ ገብረእግዚአብሔር**

አዲስ አበባ፡- ወደ ትግራይ እየገባ የሚገኘው ሰብዓዊ እርዳታ ለተቸገረው ህዝብ በትክክል እንዲደርሰው መደረግ አለበት ሲሉ የትግራይ ብልፅግና ቅርንጫፍ ፅህፈት ቤት አደረጃጀት ዘርፍ ኃላፊ አቶ ገብረፃድቅ ገብረመድህን ገለጹ፡፡

‹‹ወደ ትግራይ የገባው...ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የዋጋ ንረቱ ማርገቢያዎች፡-

## እንደበጋ ስንዴ ሁሉ ምርታማነትን ማሳደግ

## -አምራችና ተጠቃሚውን ቀጥታ ማገናኘት

ገጽ 4






# ትምህርት ሚኒስቴር ለትምህርት ጥራትና ተደራሽነት ትኩረት እንዲሰጥ ምክር ቤቱ አሳሰበ

## -የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ሊሰረቅ የቻለው በስርጭት ወቅት መሆኑን ሚኒስቴሩ ገለጸ

**አብዱረዛቅ መሐመድ**

አዲስ አበባ፡- ትምህርት ሚኒስቴር ከትምህርት ተደራሽነትና ጥራት ጋር በተያያዘ የሚነሱ የሕዝብ ጥያቄዎችን ለመመለስ ትኩረት እንዲሰጥ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት አሳሰቡ። በሌላ በኩል ትምህርት ሚኒስቴር የ2013 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ብሔራዊ ፈተና ወቅት ሊሰረቅ የቻለው በፈተና ስርጭት ወቅት መሆኑን ገልጿል።

ስድስተኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በአንደኛ ዓመት የሥራ ዘመን ስድስተኛ መደበኛ ስብሰባው የትምህርት ሚኒስቴርን የዘጠኝ ወራት ሪፖርት አዳምጧል። በወቅቱ የምክር ቤት አባላት ከትምህርት ጥራትና ተደራሽነት ጋር የተያያዙና ሌሎችም በርካታ ጥያቄዎች አንስተዋል።

የምክር ቤቱ የሰው ሀብት ልማት፣ ሥራ ስምሪትና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባሉ አቶ ፍሬው ተስፋዬ፤ የቋሚ ኮሚቴውና ከሕዝብ በቀጥታ የተላኩ ጥያቄዎችን ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የሥራ ኃላፊዎችና ተጠሪ ተቋማት አቅርበዋል።

ከ2013 ዓ.ም የትምህርት ዘመን የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ብሔራዊ ፈተና ውጤትና ከዩኒቨርሲቲ መግቢያ መቁረጫ ነጥብ ጋር በተያያዘ የተፈጠሩ ብዥታዎችን በተመለከተ ምላሽ እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል።

የምክር ቤት አባላትም፤ ከአጠቃላይ የትምህርት ጥራት፣ በገጠሪቱ የአገሪቱ ክፍሎች የትምህርት ቤቶችና የትምህርት ግብዓቶች ተደራሽ ካለመሆንና ከብሔራዊ ፈተናዎች ዝግጅትና ሕትመት ደኅንነት ጋር የተያያዙ ጥያቄዎችን አንስተዋል።

ትምህርት ሚኒስቴር በቀጣይ ጊዜያት ለትምህርት ጥራትና ተደራሽነት ትኩረት ሰጥቶ ሊሰራ እንደሚገባ ጠይቀዋል።

አክለውም፣ አሸባሪው የሕወሓት ቡድን ወረራ በፈጸመባቸውና ጦርነት በተካሄደባቸው በአማራ ክልል፣



አፋር ክልልና የኦሮሞ ብሔረሰብ ልዩ ዞን አካባቢዎች የነበሩ ተፈታኞች ከሌሎች አካባቢዎች ተማሪዎች ጋር በዕኩል መታየታቸው አግባብነት የሌለው ነው ብለዋል።

የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ በበኩላቸው፤ ሚኒስቴሩ ለትምህርት ጥራትና ተደራሽነት ትኩረት መስጠት ዋነኛ አላማው መሆኑን ገልጸዋል።

ከፈተና ስርቆት ጋር በተያያዘ ያስረዱት ሚኒስትሩ፤ የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ሊሰረቅ የቻለው በስርጭት ወቅት መሆኑን ገልጸዋል።

ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ በኢትዮጵያ በተለያየ መልኩ ብሔራዊ ፈተናዎች ሲሰረቁ መቆየታቸውን በመጠቆም፤ ፈተናው ከሚዘጋጅበት ጀምሮ ለተፈታኞች እስከሚሰጥበት ወቅት ባሉ ሂደቶች የፈተና ስርቆት ሊፈጸም ይችላል ብለዋል።

የ2013 ዓ.ም በ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ብሔራዊ ፈተና በሚሰጥበት ወቅት ስርቆት እንዳይኖር ከፈተና ዝግጅት እስከ ሕትመቱ ከፍተኛ ጥንቃቄ እንደተደረገ ተናግረዋል።

በነዚህ ሂደቶች በተደረገው ጥብቅ ቁጥጥር ምክንያት ፈተናው ሊሰረቅ የሚችልበት ዕድል በጣም አነስተኛ መሆኑን ጠቅሰው፤ ፈተናው ሊሰረቅ የቻለው በስርጭት ወቅት መሆኑን አብራርተዋል።

"ለፈታኞች ጉቦ ሰጥቶ ፈተና እንዲሰረቅ ወይም ተፈታኞች እንዲኮራረጁ የሚያደርግ ሕብረተሰብ ተፈጥሯል" ያሉት ፕሮፌሰሩ፤ ትምህርት ሚኒስትር በተቻለው መጠን የትምህርት ሥርዓት ጥራት ለማሻሻል እየሠራ ይገኛል ብለዋል።

የ2013 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል አገር አቀፍ የፈተና ውጤትን አስመልክቶ ለቀረቡ ከ30 ሺህ በላይ የተማሪዎች ቅሬታዎች ምላሽ ተሰጥቷል ያሉት ደግሞ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ተፈራ ፈይሳ ናቸው።

የብሔራዊ ፈተና ዝግጅትና ሕትመት በፌዴራል መንግሥት ደረጃ የሚከናወኑ ሲሆን እንደ 2013 ዓ.ም ከፍተኛ ጥንቃቄ የተደረገበት ጊዜ የለም ያሉት ኃላፊው፤ የፈተናው ስርጭት በክልሎች የሚከናወንና በርካታ አካላትን የሚሳተፉበት በመሆኑ ስርቆቱም የተከሰተው በዚህ ጊዜ ነው ብለዋል።

በፈተና ስርጭት ወቅት ውድ ሕይወታቸውን ያጡ የጸጥታ አካላት መኖራቸውንም አብራርተዋል።

በቀጣይ ጊዜያት መሰል ችግሮች እንዳይከሰቱ ለማድረግ ከፈተና ዝግጅት እስከ አሰጣጥ ያሉ ሂደቶችን ማሳጠር አስፈላጊ መሆኑን አመላክተዋል።

በተያያዘ ዜና፣ ምክር ቤቱ በስድስተኛ መደበኛ ስብሰባው በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የቀረበለትን የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሥልጣን የሥራ አመራር ቦርድ አባላት ሹመትን መርምሮ አጽድቋል።

በዚህም መሰረት፣ አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን የቦርዱ ሰብሳቢ እንዲሁም አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ ምክትል ሰብሳቢ ሆነው ተሹመዋል።

በተጨማሪም፣ አምባሳደር ሀሰን አብዱልቃድር፣ ዶክተር አጋረደች ጀማነህ፣ ዶክተር በድሉ ዋቅጅራ፣ ዶክተር መሳይ ገብረማርያም፣ ዶክተር ወዳጄነህ መሃረነ፣ ቀሲስ ታጋይ ታደለና ዑስታዝ ያሲን ኑሩ የቦርዱ አባል ሆነዋል።

# ዩኒቨርሲቲዎች የአገርን ብሔራዊ ጥቅም የሚያስከብሩ ዜጎች ላይ ትኩረት ሊሰጡ እንደሚገባ ተጠቆመ

## - በጐንደር ዩኒቨርሲቲ የፐብሊክ የዲፕሎማሲና ዓለም አቀፍ የጥናትና ምርምር ማዕከል ተከፈተ

**ሞገስ ተስፋ**

ጐንደር:- የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ሊያስከብሩ የሚችሉ ዜጎች ለመፍጠር ትኩረት ሰጥተው ሊሰሩ እንደሚገባ ተገለጸ። በጐንደር ዩኒቨርሲቲ የፐብሊክ የዲፕሎማሲና ዓለም አቀፍ የጥናትና ምርምር ማዕከል ተከፈተ።

በጐንደር ዩኒቨርሲቲ አዘጋጅነት "የአባይ ሕብረ ዝማሬ" የተሰኘ የመዝሙር ሲዲ ምርቃትና የፐብሊክ ዲፕሎማሲና ዓለም አቀፍ የጥናት ማዕከል የማስጀመሪያ መርሐግብር ትናንት ተካሂዷል።

በወቅቱ የጐንደር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት አስራት አጸደወይን (ዶክተር) እንደገለጹት፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለአገሩ ብሔራዊ ጥቅም ዘብ የሚቆብ ብቁ ዜጋ ለማፍራት ትኩረት ሊሰጡ ይገባል።

በዕውቀትና በክህሎት ብቁ የሆነ ዜጋ መፍጠር ሲቻል ለአገሩም ዋስ ጠበቃ ሆኖ በዓለም አቀፍ መድረክ መከራከር ይችላል። በዚህ ረገድ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ የእራሱን አስተዋጽኦ ለማበርከት ጥረት እያደረገ ይገኛል ብለዋል።

በህዳሴው ግድብና በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል በተከሰተው ጦርነት ዓለም አቀፍ ጫናው ከፍተኛ ነበር። ጫናውን ለመመከት የትምህርት ተቋማት ጠንካራ ዲፕሎማትና የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ሥራ መስራት የሚችል ዜጋ ለመፍጠር በሚጠበቅባቸው ልክ መስራት ይጠበቅባቸዋል ሲሉ ዶክተር አስራት አክለዋል።

ዩኒቨርሲቲው ያቋቋመው የዲፕሎማሲና ዓለም አቀፍ ግንኙነት የምርምር ማዕከሉ በጥናትና ምርምር፣ በትምህርትና ስልጠና እንዲሁም ህዝባዊ አገልግሎት ላይ በትኩረት ይሰራል ብለዋል።

የጐንደር ዩኒቨርሲቲ የፐብሊክ የዲፕሎማሲና ዓለም አቀፍ የጥናትና ምርምር ማዕከል ማስጀመሩ የአገራቸውን ብሄራዊ ጥቅም ማስከበር የሚችሉና ተመራማሪዎችን ለማፍለቅ ያግዛል ሲሉ ፕሬዚዳንቱ ተናግረዋል።

በኢትዮጵያ የሚገኙ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በሰላምና ደህንነት ዙሪያ፣ በዲፕሎማሲው ዘርፍ፣ የሚታዩ አለመግባባቶችን ለመፍታት በሚጠበቅባቸው ልክ እየሰሩ አይደለም ያሉት የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት፤ ይህ ሊታረምና መስተካከል የሚገባው ጉዳይ መሆኑን ጠቁመዋል።

የጐንደር ዩኒቨርሲቲ ከመማር ማስተማሩ ሂደት ጐን ለጐን ኢትዮጵያ እየገነባችው ባለው በታላቁ የህዳሴ ግድብ ፍትሀዊ ተጠቃሚነት ዙሪያ ከህግ አንጻር እንዴት መቃኘት እንዳለበትና በሌሎች አገራዊ ጉዳዮች ላይ በከፍተኛ ኃላፊነት በርካታ ሥራዎችን እየሰራ መሆኑን አስራት አጸደወይን(ዶክተር) ገልጸዋል።

በመድረኩ ላይ የተገኙት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አምባሳደር ዲና ሙፍቲ እንደገለጹት፣ በአሁኑ ሰዓት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም ላይ ያነጣጠረና ሉዓላዊ ክብሯን ለመዳፈር ዓለም አቀፍ ጫና የበረታበት ጊዜ ነው።

ኢትዮጵያም ብሔራዊ ጥቅሟን ለማስከበር እንደ ጐንደር ዩኒቨርሲቲ ካሉ የከፍተኛና የምርምር ተቋማት ብዙ ውጤት ትጠብቃለች ሲሉ ተናግረዋል።

ጎንደር ዩኒቨርሲቲ በአገራችን የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ታሪክ ገናና ስም ካላቸው አንጋፋ ዩኒቨርሲቲዎች አንዱ የሆነው ጐንደር ዩኒቨርሲቲ ከግማሽ ምዕተዓመት በላይ በዘለቀ ዘመኑ በርካታ ምሁራንን ለአገር አበርክቷል



ዶክተር አስራደ አጸደወይን



አምባሳደር ዲና ሙፍቲ

ብለዋል።

ተቋሙ ማህበራዊና አገራዊ ተልዕኮውን በሚገባ እየተወጣ ያለ ተቋም ነው። በማህበራዊ አገልግሎቱ ለአካባቢው ማህበረሰብ ተጨባጭ ሥራ በመስራት ዕውነተኛ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም መሆኑን በተግባር ያሳየን የሕዝብ ተቋም ነው ሲሉም አምባሳደር ዲና ገልጸዋል።

እንደ አምባሳደር ዲና ሙፍቲ ገለጻ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አንዳንድ አገራት በኢትዮጵያ ላይ እያደረጉ ያሉትን ኢ ፍትሃዊ ጫና ለመመከት ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር መስራት ወሳኝ መሆኑን ያምናል።

ይህን መሰረት በማድረግ በሁሉም የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ማእከል እየተቋቋመ ነው ብለዋል።

የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም በአግባቡ የሚያስከብሩ ልጆችን ከማዕከላቱና ከዩኒቨርሲቲው ማፍራት ይጠበቅብናል ሲሉም መልዕክት አስተላልፈዋል።

በመድረኩ በጐንደር ዩኒቨርሲቲ አዘጋጅነት "የአባይ ሕብረ ዝማሬ" በሚል የተመረቀውን የመዝሙር ሲዲ ለታላቁ ህዳሴ ግድብ ሕዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ምክር ቤት ጽህፈት ቤት ምክትል ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ ፍቅርተ ታምር ተረክበዋል።



ዶክተር መሐመድ ኡስማን

## ዩኒቨርሲቲው በጦርነቱ የደረሰውን ጉዳት መለየት የሚያስችል ጥናት እያደረገ መሆኑን ገለጸ

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ:- ጦርነቱ በአካባቢው ማህበረሰብ ያደረሰውን ቁሳዊና ሰብአዊ ጉዳት መለየት የሚያስችል ጥናት እያደረገ መሆኑን ሰመራ ዩኒቨርሲቲ ገለጸ።ጉዳት ለደረሰባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች የሰብአዊ ድጋፍ እያደረገ መሆኑንም አመልክቷል።

የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር መሐመድ ኡስማን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ዩኒቨርሲቲው በጦርነቱ በአካባቢው ማህበረሰብ ያደረሰውን ቁሳዊና ሰብአዊ ጉዳት ለመለየት ጥናት እየሰራ ነው።

የተደራጀ ታጣቂ ኃይል ደሃ የአርብቶ አደር ማህበረሰብን ዘርፏል፣ በከባድ የጦር መሳሪያ ጉዳት አድርሷል ያሉት ዶክተር መሐመድ፤ ጦርነቱ በአካባቢው ማህበረሰብ ያደረሰውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን፣ በክልሉ ታሪካዊ ቅርሶች እና በቱሪዝም ዘርፍ፣ በመንግሥት ተቋማት ላይ፣ በሕብረተሰቡ ስነ ልቦና ላይ የደረሰውን ጉዳት የሚለይ አጠቃላይ ጥናት እያካሄዱ እንደሚገኙ ጠቅሰዋል።

በሌላ በኩል በማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎት በጦርነቱ ለተፈናቀሉና ጉዳት ለደረሰባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ፈጣን የሰብአዊ ድጋፍ በመስጠት ትኩረት ሰጥተው እየሰሩ መሆናቸውን አመልክተዋል።

ባለፉት ስድስት ወራት 25 ዩኒቨርሲቲዎችን በማንቀሳቀስ ለሰብአዊ ድጋፍ የሚውል 75 ሚሊዮን ብር የሚገመት የአይነት እና የገንዘብ ድጋፍ ማሰባሰብ መቻሉን አውስተው፤ መምህራን፣ የዩኒቨርሲቲው ሰራተኞች እና ተማሪዎች አቅማቸው በፈቀደ መጠን ድጋፍ እያደረጉ እንደሚገኙም ተናግረዋል።

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ በክልሉ ውስጥ በጦርነቱ ምክንያት የተፈናቀሉ በርካታ ማህበረሰቦች አሉ።ሕብረተሰቡ በጦርነት አካባቢ የሚኖር እንደመሆኑ የሰብአዊ ድጋፍ አገልግሎት እየሰጠን እንገኛለን።

ሕጻናት፣ ሴቶች፣ ነፍሰ ጡሮችንና አረጋውያንን በማገዝ ኃላፊነታችንን እየተወጣን ነው ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ በየሕክምና ተቋማት በመገኘት የጤና አገልግሎት እያዳረሱ መሆኑንም ጠቁመዋል።

ከስርዓተ ትምህርት ጀምሮ የክልሉን የትምህርት ዘርፍ እያገዝን ነው። መማር ማስተማሩ ከክልሉ የቱሪዝም ዘርፍና ከተፈጥሮ ማዕድን ጋር እንዲያያዝ በማድረግ ላይ ነን ብለዋል።

በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች አጠቃላይ የሚባሉና አንድ አይነት ሥራ የሚሰሩ፣ በአንድ አይነት ስርዓተ ትምህርት የሚያስተምሩ፣ በአንድ አይነት ጉዳይ ተቋም የሚመሰረቱ እንደነበሩ አስታውሰው፤ አሁን የተለየ ትኩረት ተሰጥቷቸዋል፣ በተለዩበት ዘርፍ ትኩረት ማድረጋቸው ውጤት እንዲያስመዘግቡ ያስችላቸዋል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ሰመራ ዩኒቨርሲቲም የአካባቢውን እምቅ ሃብት መሰረት በማድረግ በጂኦሎጂ፣ በግብርና እና በቱሪዝም ዘርፎች ትኩረት አድርጎ እንዲሰራ መለየቱንም አስታውሰዋል።በአካባቢው ባለው ሃብት በመጠቀም ለመለወጥና ለችግሮች መፍትሄ ለማበጀት እንደሚያግዘው አመልክተዋል፡፡

‹‹የተለየ ትኩረት መያዛችን በልዩ ትኩረት እንድንሰራ ያግዘናል። የሃብት ብክነትን ለማዳን፣ በዘርፋችን ብቃት ያለው ባለሙያ ለማፍራት ያስችለናል›› ብለዋል።በቱሪዝም ዘርፍ የምናሰለጥናቸው ባለሙያዎች ኤርታሌንና የአካባቢውን ታሪካዊ ቅርሶች እያዩ ለመማር ያግዛቸዋል፣ ምርምሮቻችን ችግር ፈቺዎች ለማድረግ እንደሚያግዝም ጠቁመዋል።

በአካባቢው የሚገኘውን ጨው በሰለጠነ የሰው ኃይል፣ በቴክኖሎጂና በምርምር በመደገፍ እንዲሁም በማህበረሰቡ ውስጥ የሚገኙ እውቀቶችን በመጠቀም በተሻለ መንገድ እንዲመረት ለማድረግ፣ በአዮዲን የበለጸገ፣ ጥራቱን የጠበቀ፣ ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚውል በቂ ምርት ለማምረት ያስችላል።

በተመሳሳይ በአካባቢው የሚገኘውን የፖታሽ ምርት በማውጣት ለማዳበሪያ እንዲውል፣ ለውጭ ገበያ በማቅረብ የውጭ ምንዛሪ እንዲያስገኝ ለማድረግ እንደሚያስችልም ተናግረዋል።

ሰመራ ዩኒቨርሲቲ ከተመሰረተ 13 ዓመታትን ያስቆጠረ ሲሆን፤ ሁለተኛው ጀነሬሽን ከሚባሉት ውስጥ ይመደባል።የሰለጠነ የሰው ኃይል በማፍራት፣ በምርምር ዘርፍና በማህበረሰብ አገልግሎት የተለያዩ ተግባራትን ሲያበረክት መቆየቱ ይታወቃል።

# የኑሮ ውድነቱ በተቀጣሪዎች ላይ እያሳደረ ያለው ጫና አሳሳቢ መሆኑ ተገለጸ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ:- በኢትዮጵያ እየተስተዋለ ያለው የኑሮ ውድነት በተቀጣሪዎች ላይ በተለይም ደግሞ ዝቅተኛ ደመወዝ በሚከፈላቸው ሠራተኞች ላይ እያሳደረ ያለው ጫና አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱን የኢትዮጵያ ሠራተኛ ማኅበራት ኮንፌዴሬሽን(ኢሠማኮ) አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ ሠራተኛ ማኅበራት ኮንፌዴሬሽን ጠቅላይ ምክር ቤት 48ኛ መደበኛ ስብሰባውን ትናንት ሲያካሂድ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የኮንፌዴሬሽኑ ፕሬዚዳንት አቶ ካሣሁን ፎሎ እንዳሉት፤ አሁን ላይ በኢትዮጵያ እየተስተዋለ ያለው የኑሮ ውድነት ሠራተኛው ላይ ከፍተኛ ችግር ፈጥሯል። በተለይም ዝቅተኛ ደመወዝ የሚከፈላቸው ሠራተኞች ላይ የኑሮ ጫናው አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል ፡፡

ኢንዱስትሪ ፓርኮችን ጨምሮ በርካታ ድርጅቶች ለሠራተኞች የሚከፍሉት ደመወዝ እጅግ ዝቅተኛ መሆኑን ያስታወሱት አቶ ካሣሁን፤ እነዚህ ሠራተኞች በሚከፈላቸው ደመወዝ ሕይወታቸውን ለመምራት አዳጋች እንደሆነባቸውም ጠቁመዋል።

በአሠሪና ሠራተኛ አዋጁ መሠረት ዝቅተኛውን የደመወዝ ወለል የሚወስን ደንብና የደመወዝ ቦርድ ተቋቁሞ እንደ አገር ዝቅተኛ የደመወዝ ወለል መቀመጥ እንዳለበት የጠቆሙት ፕሬዚዳንቱ፤ አዋጁ የወጣው



አቶ ካሣሁን ፎሉ

ከሁለት ዓመት በፊት ቢሆንም እስካሁን ድረስ ደንቡ ወጥቶ ወደ ሥራ ባለመግባቱ በተለይም ዝቅተኛ ደመወዝ የሚከፈላቸው ሠራተኞች ላይ የኑሮ ውድነቱ ጫና እያሳደረ መሆኑን ገልጸዋል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ የተከሰተው ኮቪድ 19፣ በአገራችን ያለው ጦርነትና በቅርቡ በሩስያና ዩክሬን መካከል እየተካሄድ ያለው ጦርነት ኑሮ ውድነቱን በማባባስ በኩል ትልቅ ሚና እንዳላቸው የተናገሩት አቶ ካሣሁን፤ የኑሮ ውድነቱ እንዳለ ሆኖ ከውጭ ምንዛሪ እጥረትና በሌሎችም ችግሮች ምክንያት ድርጅቶች ሠራተኞችን እየቀነሱ በመሆኑ መንግሥት በተቻለ መጠን ለድርጅቶች የውጭ ምንዛሪ በመፍቀድና ሌሎችንም አስፈላጊ እገዛዎችን በማድረግ ሠራተኞች እንዳይቀንሱ ማድረግ ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

አሁን ላይ አንዳንድ ሠራተኞች ያለ ምግብ ሥራ ላይ ስለሚውሉ ድንገት ራሳቸውን ስተው የመውደቅ አደጋ ሁሉ እየገጠማቸው እንደሆነ መረጃዎች መኖራቸውን ጠቁመው፤ በልቶ ማደር ካልተቻለና ነገሮች በዚህ መልኩ የሚቀጥሉ ከሆነ የኢንዱስትሪ ምርታማነታችን ፈተና ላይ መውደቁ አይቀርም፡፡ከዚህ አኳያ መወሰድ የሚገባቸውን አፋጣኝ እርምጃዎች በመውሰድ የኑሮ ውድነቱን ጫና ለመቀነስ መሠራት እንዳለበትም አስረድተዋል።

በሌሎች አገሮች ልምድ ኑሮ ውድነቱ ሲጨምር ዝቅተኛ ደመወዝ ወለል እንዲሻሻል እንደሚደረግ ጠቅሰው፤ በእኛ አገር ይህን ማድረግ ይቻል ዘንድ የዝቅተኛ ደመወዝ ወለል መወሰኛ ደንብ በአፋጣኝ ወጥቶ ዝቅተኛው የደመወዝ ወለል እንዲቀመጥ መደረግ እንዳለበት አስገንዝበዋል።

የኑሮ ውድነቱን ከሚያባብሱት ነገሮች አንዱ አገሪቱ ላይ ዘላቂ ሰላም አለመስፈኑ ነው ያሉት አቶ ካሣሁን፤ በኢትዮጵያ አስተማማኝ ሰላም ሰፍኖ ዜጎች በሰላም ወጥተው እንዲገቡ መንግሥት ሰላምን በማስፈን ረገድ በቁርጠኝነት መሥራት ይኖርበታል ብለዋል፡፡

# በወሳኝ ኩነት አገልግሎት አሰጣጥ ተማርረናል ሲሉ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ተናገሩ

## - ችግሩ አገልግሎቱ በቴክኖሎጂ ባለመደገፉ የተከሰተ መሆኑን ጽህፈት ቤቶቹ ገልጸዋል

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ:- በወሳኝ ኩነት አገልግሎት አሰጣጥ ባለሙያዎቹ የአገልጋይነት መንፈስ ባለመላበሳቸው በሚደርስባቸው መጉላላትና እንግልት መማረራቸውን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነዋሪዎች ተናገሩ።ችግሩ አገልግሎቱ በቴክኖሎጂ ባለመደገፉ የተከሰተ መሆኑን ጽህፈት ቤቶቹ ገልጸዋል።

የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02 ነዋሪ ወይዘሮ ታደለች ከበደ፤ በወረዳው የወሳኝ ኩነት አገልግሎት አሰጣጥ ፈጣን አለመሆንና የአገልጋይነት መንፈስ አለመላበስ ሳቢያ መማረራቸውን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

በሚደርሰው መጉላላትና የአሰራር ግልጽነት መጓደል የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥ በአግባቡ እንዳናገኝ አድርጓል።ችግሩ አገልግሎቱ በቴክኖሎጂ ባለመደገፉ ምክንያት የተከሰተ አይደለም።በጉዳይ አስፈጻሚ በኩል የማስጨረስ ሁኔታዎችም ይስተዋላሉ ብለዋል።ይህም ተገልጋዮች በወቅቱ አገልግሎት እንዳናገኝና እንድንገላታ እያደረገ ነው ብለዋል።

ወረዳው ካለው ስፋትና የህዝብ ብዛት ጋር ተዳምሮ የውስጥ አሰራር ችግሮች ይበዙበታል።በሰራተኞችም የአገልጋይነት መንፈስ አለመላበስ ይስተዋላል ሲሉም ወይዘሮ ታደለች ተናግረዋል፡፡

የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 ነዋሪ አቶ ግርማ ተክሉ በበኩላቸው፤ በወረዳው የወሳኝ ኩነት አገልግሎት ባለሙያዎች በሥራ ሰዓት በሥራ ቦታቸው አለመገኘት፣ የሥራ ሰዓትን በስብሰባ ማሳለፍ፣ ተገልጋይን ማጉላላት፣ መብራትና ሲስተም የለም በሚል አገልግሎቱን ማቋረጥና ነዋሪውን ማጉላላት የወረዳው መገለጫ ነው ብለዋል፡፡

ሰራተኞች የአገልጋይነት መንፈስን የተላበሱም አይደሉም፣ የውስጥ ሰራተኞች አገልግሎቱን በጉዳይ አስፈጻሚ በኩል እንዲፈጸምልን የመወትወት ጉዳይ ሌላኛው ችግር እንደሆነ አቶ ግርማ ተናግረዋል፡፡

የአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 ነዋሪ ወይዘሮ እፀገነት ግርማ በበኩላቸው፤ ወረዳው በአጠቃላይ የአገልጋይነት መንፈስ መጓደል ይስተዋልበታል።ችግሮቹም እየባሱ እንጂ እየተሻሻሉ አይደሉም።አመራሩ ስብሰባ ያበዛሉ፣ አገልግሎቱንም ዞረው አያዩም።

እንደ ወይዘሮ እፀገነት ገለፃ፤ በወረዳው የጤና መድህን፣ የሴፍቲኔት፣ የድጋፍና እርዳታ አገልግሎቶችን ተጠቃሚው የሚሆነው እጀ ረጅምና ከውስጥ ሰው



ያለው ብቻ ነው፡፡

አገልግሎትን ለማግኘት ወደ ወረዳው የሚሄደው ተገልጋይም ጉዳዩን ጥሎ ነው፣ ፈጣን አገልግሎት አግኝቶ ወደ ጉዳዩ ለመመለስ ይፈልጋል ነገር ግን ሰራተኞች በወቅቱ በሥራ ገበታቸው ባለመገኘታቸው እነሱን በመጠበቅ በከንቱ ጊዜውን ያጠፋል ብለዋል ወይዘሮ እፀገነት።

ሰራተኞች በሥራ ሰዓት ቢሮ ተቀምጠውም ጊዜያቸውን የሚያጠፉት በሶሻል ሚዲያ ሲመለከቱ ነው።አንዱ እየሰራ ሌላው ይቀመጣል፣ በተመሳሳይ ሰዓት ሁሉም ሥራቸውን አይሰሩም፡፡ሲስትም የለምና ተበላሽቷል በሚል ያለሥራ መቀመጥም ይስተዋላል ብለዋል፡፡

የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02 ወሳኝ ኩነት ጽህፈት ቤት ኃላፊ ወይዘሮ ሽብሬ ድሪባ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ችግሩ አገልግሎቱ በቴክኖሎጂ ባለዘመኑና ተግባሩን በአነስተኛ የሰው ኃይል የሚሰራ በመሆኑ የተከሰተ ነው።

ዘመናዊ ባለመሆኑም የነዋሪዎችን ፋይል በመፈልግ ጊዜ እየወሰደብን በቀን የአገልግሎት ፈላጊውን ሳናዳርስ ለቀጣይ ጊዜ ቀጥረን የምናስመልስበት ሁኔታም አለ።አገልግሎቱ በአስቸኳይ አዋጅ ታግዶ መቆየቱም ችግሩ እንዲባባስ አድርጓል።

ከልደት፣ ጋብቻ፣ የሞት ምዝገባንና ማስረጃ አገልግሎትን ሳይጨምር መታወቂያ ብቻ በቀን እስከ 250 ነዋሪዎችን እያስተናገዱ መሆኑን፣ ችግሩን ለመቅረፍም ቅዳሜን ጨምሮ አመራሩና ሰራተኛው በእረፍት ቀኑ እየሰራ መሆኑን ወይዘሮ ሽብሬ ገልጸዋል።

ወይዘሮ ሽብሬ በገለጻቸው፣ የሚስተዋለው ሰልፍ፣ መጉላላትና እንግልት ቀጣይነት ባለው አሰራር ለመቅረፍ እየሰራን ነው።ከአመራሩ ጋርም በመነጋገርና በጀት በማስመደብ በቴክኖሎጂ ለማዘመን እንደታሰበም ጠቁመዋል፡፡

የአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 የወሳኝ ኩነትና የነዋሪዎች መታወቂያና አገልግሎት ቡድን መሪ አቶ ደምስ ጥበበስላሴ ካሳሁን፤ ነዋሪው በሚመቻቸው ጊዜ አገልግሎት እንዲያገኙ በማሰብ በቀጠና የነበረውን በመጡበት ቅደም ተከተል በማድረግ ነዋሪዎቹ በሚመቻቸው ቀን እንዲገለገሉ አድርገናል፡፡

በከተማ ደረጃ የመረጃ ቋቱ ህዝቡ በአገልግሎት እጦት እንዳይጉላላ ለማድረግ የመረጃ ማዕከሉ እስኪስተካከል ድረስ በማንዋል እየሰራን ነው።አገልግሎቱን ፈልጎ የሚመጣው ነዋሪ ቁጥር ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ በሰራተኞች ላይ የሥራ ጫና ፈጥሯል ሲሉ አብራርተዋል።

በዚህም አልፎ አልፎ የነዋሪዎችን መረጃ በትክክል ያለመሙላት፣ የተጠየቀውን አገልግሎት በተገቢው አለመስጠትና መሰል ስህተቶች ይስተዋላሉ።ሰራተኞች በሥራ ሰዓት ከሥራ ገበታ ይጠፋሉ።ሥራቸውን የገቢ ምንጭ አድርገውታል የሚባለው ግን መሰረተ ቢስ ነው።ሲስተም ጠፍቶ እንኳን በማንዋል እየሰራን ነው ብለዋል አቶ ደምስ በገለጻቸው፡፡

ዜና

# የዋጋ ንረቱ ማርገቢያዎች፡-

## እንደበጋ ስንዴ ሁሉ ምርታማነትን ማሳደግ

## -አምራችና ተጠቃሚውን ቀጥታ ማገናኘት

ጌትነት ተስፋማርያም



ፎቶ ገባቦ ገብሬ

በየሕዝባዊ መድረኮች መወያያ ሆኖ የሰነበተው የመሰረታዊ ፍጆታዎች የዋጋ ንረት ከሰሞኑ በምክር ቤቱ ቋሚ ስብሰባ ሰፊ ክርክር ያስተናገደ ጉዳይ እንደነበር ይታወሳል። ትናንትና ደግሞ የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት ባዘጋጀው የአዲስ ወግ መድረክ የኑሮ ውድነት ጉዳይ ዋነኛ የመወያያ ርዕሰ አጀንዳ ሆኗል። "የኑሮ ውድነት መንስኤዎቹ እና የመፍትሔ ርምጃዎች" በሚል ርዕስ ምሁራንና የዘርፉ ባለሙያዎች የተለያዩ ሃሳቦችን አንስተዋል።

በወቅቱ የፕላን እና ልማት ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ነመራ ገበየሁ፤ የዋጋ ንረቱ የብዙ መንስኤዎች ድምር ውጤት ነው፤በዋናነት የሕዝብ ቁጥር ሲበዛ በዚያው ልክ የምርት አቅርቦት አለማደጉ ለችግሩ መነሾ ሆኗል ሲሉ አስረድተዋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር እያደገ ነው፤ በዚያው መጠን ከተሜነትም ሲስፋፋ የመሰረታዊ ፍጆታ ዕቃዎች ፍላጎትም አድጓል ያሉት ዶክተር ነመራ፤ ይሁንና ከኢትዮጵያ የፍላጎት አቅርቦት ውስጥ አንድ ሶስተኛው ብቻ ከኢንቨስትመንትና ከተያያዥ ልማት የሚሟላ ሲሆን ቀሪው ሁለት ሶስተኛ ፍላጎት ለማሟላት ግን ከውጭ ምርቶችን እናስገባለን ብለዋል።

ይሄንን ፍላጎት የሚመጥን ምርት በአገር ውስጥ ማዘጋጀት ባለመቻላችን በዓለም ኢኮኖሚ ጫና ውስጥ የወደቀ የዋጋ ንረትን በተለይም በምግብ ፍጆታዎቻችን ላይ እንደተስተዋለ ነው የሚናገሩት።

የምግብ ፍጆታዎች ዋጋ መናር ብዙዎችን ጎድቷል ያሉት ዶክተር ነመራ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ አንድ ቤተሰብ ከሚያገኘው ገቢ ውስጥ በአማካይ በመቶውን ለምግብ ፍጆታዎች ግዥ ያውላል። የእነዚህ ምርቶች ዋጋ ሲንር የተጠቃሚውም ኢኮኖሚ እንደሚናጋም ነው የሚገልጹት።

ለአብነት ስንዴን ብንወስድ ቀደም ባሉ ዓመታት 25 በመቶ ፍጆታችን ከውጭ ነው የምናስመጣው፤ አሁን ደግሞ ጦርነት፣ ድርቅ መፈናቀልና የዓለም ወቅታዊ ሁኔታ ተደምሮ የስንዴ ዋጋውን እንዲንር አድርጎታል። ይህም በዳቦና በተለያዩ ምግቦች ላይ ተጽዕኖው ከፍተኛ ሆኗል ብለዋል።

መፍትሔውም ምርትን ማሳደግ ወይም በሌላ አገላለጽ ምርትን ከሕዝብ ቁጥርና ፍላጎት ጋር እንዲጣጣም ማድረግ ያስፈልጋል። የግብርና ምርቶችን ወይም የምግብ ፍጆታ ሸቀጦችን በብዙ ዕጥፍ ማሳደግ አለብን ሲሉ አስረድተዋል።

በብሔራዊ ባንክ ከፍተኛ የማክሮ ኢኮኖሚ አማካሪው አቶ መለሰ ምናለ በበኩላቸው እንደሚገልጹት ፤ጤናማ የሆኑ የዋጋ ጭማሪ በአደጉት አገራትም አለ። የዋጋ ንረት ግን የገዥውን ማኅበረሰብ የመግዛት አቅም የመሸርሸር ድርጊት ነው።

በኢትዮጵያም ባለፉት 20 ዓመታት በየወቅቱ 15 በመቶና ከዚያ በላይ የሆነ የዋጋ ግሽበት ተከስቷል።

ምርቶች በበቂ ሁኔታ አለመመረታቸው፤ የምርት ስርጭትና ግብይት ጉድለት፣ የበጀት አስተዳደር ጉድለት እንዲሁም ዓለም አቀፍ ሁኔታዎችም የኑሮ ውድነቱን የሚያባብሱ ዋነኛ ምክንያቶች ሆነዋል ሲሉ ያስረዳሉ።

የዋጋ ንረት ዋነኛው መለኪያው የማክሮ ኢኮኖሚ ዝንፈት ነው ያሉት አቶ መለሰ፤ ይህን ችግር ለማስተካከል መንግሥት የኢኮኖሚ ሪፎርም በማድረግ በቀጥታ ከብሔራዊ ባንክ ከመበደር ይልቅ ገበያ መር የሆነ የግምጃ ቤት ሰነድ በማቅረብ ገበያ ውስጥ ያለውን ገንዘብ መልሶ ለመጠቀም ጥረት አድርጓል ይላሉ።

በተጨማሪ ከውጭ በዝቅተኛ ወለድ ብድር በመውሰድ ኢኮኖሚውን ለመደጎም መጣሩን ይገልጻሉ።

ይህ ዕርምጃ ለጊዜውም ጥሩ ውጤት ያመጣ ቢሆንም በኢትዮጵያ የተከሰተው ጦርነት፤ ድርቅና መፈናቀል እንዲሁም ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎች ማለትም የኮሮና ቫይረስ መከሰትና የሩሲያና ዩክሬን ጦርነት ችግሩን አባብሰውታል።

መንግሥትም ጫናውን ለመቀነስ ከብሔራዊ ባንክ ብድር ወደ መውሰድ ገብቷል። ይህም የዋጋ ንረቱን አባብሶታል ሲሉ ያስረዳሉ።

መፍትሔው ልክ እንደበጋ ስንዴው ተሞክሮ ሁሉ ምርታማነትን እያሳደጉ መሄድ ነው። በዋናነትም ግን ዓለም አቀፋዊ ምክንያት ያለውን የዋጋ ንረት ተረዳድተን ማለፍ አለብን ሲሉ ምክረ ሃሳባቸውን ለግሰዋል።

በኢትዮጵያ ሕብረት ሥራ ኮሚሽን የሕብረት ሥራ ግብይት ዳይሬክተሯ ይርጋለም እንየው፤ አገራችን ያለው የግብይት ሰንሰለት ርዝማኔው ካልተሻሻለ የዋጋ ንረትም መከላከል ያዳግታል ሲሉ መከራከሪያቸውን አቅርበዋል።

በኢትዮጵያ ከ19ሺህ 600 በላይ የሕብረት ሥራ ማሕበራት ቢኖሩም አብዛኛው ምርት ግን ለተጠቃሚው የሚቀርበው በህገወጥ የዋጋ ተማኞች በኩል መሆኑን አስታውቀዋል።

የሕብረት ሥራ ማሕበራትና በርካታ የሸማቾች ማሕበራት ቢኖሩም እሴት የማይጨምሩ ሕገወጥ የግብይት ተዋናዮች መኖራቸው ተገቢው የዋጋ ተመን እንዳይኖር አድርጓል ይላሉ።

አርሶ አደሩም ሆነ መንግሥት የምርቶች ዋጋ ተመን እየሰጡ አይደለም፤ ይልቁንም በገበያ ሰንሰለቱ ውስጥ ያሉ ህገወጦች ናቸው እንደፈለጉት ዋጋ የሚተምኑት ሲሉ ያስረዳሉ።

አንድ ምርት ከአርሶአደሩ እስከ ተጠቃሚው እስኪደርስ በርካታ የዋጋ ሰንሰለቶች አሉ፤ እነዚህን ረጅም ሰንሰለቶች በመቁረጥ በቀጥታ አምራችና ሸማች የሚገናኙባቸውን ሰፋፊ ማዕከላት መገንባት እንደሚያስፈልግ ይጠቁማሉ።

ልክ እንደ ጃፓን ሁሉ በየአካባቢው የመሰረታዊ ፍጆታ ምርቶች ገበያ ማዕከላትን በማቋቋምና፤ ሳምንታዊ የግብርና ውጤቶች መሸጫ ባዛሮችን በየአካባቢው በመዘርጋት የዋጋ ንረቱን ማረጋጋት ይቻላል የሚል ሃሳብ አቅርበዋል።

እንደ ዳይሬክተሯ ከሆነ፤ ለችግሩ ዘላቂ መፍትሔ ለማበጀት የግብይት ሰንሰለቱን ማሳጠር፤ ምርታማነትን ማሳደግ፣ የአቅርቦት ክፍተትን መሙላት፣ የአምራችና የኢንዱስትሪ ትስስርን ማጠናከር፣ የሕብረት ሥራ ማኅበራትን አሠራር ማዘመን ያስፈልጋል።

# "የፐብሊክ ዲፕሎማሲው...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ዜጋ በፐብሊክ ዲፕሎማሲ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ እንደሚኖርባቸው ተናግረዋል። መደበኛው የዲፕሎማሲ ተግባር ውጤታማ እንዲሆንም በፐብሊክ ዲፕሎማሲ ሊታገዝ ይገባል ብለዋል።

ለገጽታ ግንባታ፣ ለኢኮኖሚ ልማትና ለፖለቲካ አላማዎች ስኬት የፐብሊክ ዲፕሎማ ሥራ ወሳኝ መሆኑን አውስተው፤የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ለመደበኛው ዲፕሎማሲ ሥራ አጋዥ መሆኑን እና በአሁኑ ጊዜም የውጭ ተጽዕኖን ከመቋቋም አንጻር አስፈላጊ መሆኑን ጠቅሰዋል።

አምባሳደሩ በመግለጫቸው እንዳስታወቁት፣ የፐብሊክ ዲፕሎማሲው በአገሪቱ የተደቀነውን ዓለም አቀፍ ጫና ለመቋቋም በመሆኑ ይህንኑ ለማጠናከርም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የጎንደር ዩኒቨርሲቲን ጨምሮ በአምስት የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ማእከል መከፍቱን አመልክተዋል ።

በሌላ በኩል ባለፈው ሳምንት 20 ሰብዓዊ ድጋፍ የጫኑ ተሽከርካሪዎች ወደ ትግራይ የገቡ መሆኑን አስታውሰው፥ መንግሥትም ይህን ድጋፍ ለማስቀጠል ዝግጁነቱ እንዳለው ቃል አቀባዩ አመላክተዋል። ነገር ግን ህወሓት በእርዳታ አቅርቦት ሂደቱ ላይ ችግር እየፈጠረ መሆኑን አስረድተዋል።

በኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመቅረፍ እና እድልን ለማስፋት መሰራቱን ያነሱት ቃል አቀባዩ፣ በእስራኤል የቱሪዝም አውደ ርዕይ መካሄዱን ተናግረዋል።

በህንድ የአፍሪካ ንግድ ፎረም መካሄዱን በመጠቆም በአንካራ እና ሱዳን መሰል የኢኮኖሚ ሥራዎች መሰራታቸውን አብራርተዋል።

ከትናንትና በስቲያም የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር እና ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን በአሜሪካ እና አውሮፓ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ጋር በወቅታዊ ሁኔታ ላይ መወያየታቸውንም ጠቁመዋል።

የጂቡቲው ፕሬዚዳንት እስማኤል ዑመር ጌሌ በኢትዮጵያ ያደረጉትን ጉብኝት እና የነበሩ ሁነቶችን በተመለከተም ማብራሪያ ሰጥተዋል።

በሰሜን አሜሪካ የሚገኙ አምባሳደሮችም ኤች አር 6600 ረቂቅ ህግ እንዳይፀድቅ የዲፕሎማሲ ሥራ መስራታቸውን አስረድተዋል።

በመግለጫቸው ኤርትራ በኢትዮጵያ ከአም ባሳደር ደረጃ ጉዳይ አስፈጻሚ መመደቧ በአገራቱ ግንኙነት ላይ የሚያመጣው ለውጥ የለም ብለዋል። ሀገራቱ ያላቸው ግንኙነትም ጤናማ መሆኑን አረጋግጠዋል።

መንግሥት አምነስቲና ሂውማን ራይት ዎች እውነቱን ማወቅ ከፈለጉ በጥልቁ እንዲመረምሩ መክረዋል፡፡

## ህወሓት በወልቃይት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በኋላ ልዩነት እንዲፈጠር ተሰርቷል።

የወልቃይት ጠገዴና ጠለምት አካባቢዎች በድሮው ጎንደር አውራጃ ስር የነበሩ ሲሆን፤ ህወሓት በ1984ዓ.ም ስልጣን ከያዘ በኋላ አካባቢውን በጉልበት ወደ ትግራይ ክልል እንዲዋሰን በማድረግ ህዝቡን እንዲፈናቀልና በአሰቃቂ ሁኔታ በጅምላ በማሰር የዘር ጭፍጨፋ እንዲፈጸም አድርጓል ነው ያሉት፡፡

የጠለምት ነዋሪ አቶ ዘውድነህ አስፋው በቁመቱ ልክ ጉድጓድ በመቆፈርና በመቅበር በአሰቃቂ ሁኔታ እንዲሞት መደረጉን ከቤተሰቡ የተገኘውን መረጃ መሰረት በማድረግ የጥናት ቡድኑ ለአብነት ጠቅሷል።

በቅርቡ በተገኙት 12 የጅምላ መቃብሮች ቤተሰቦቻቸው አይናቸው እያየ የተቀበሩባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ቤተሰቦቻቸው የት እንደተቀበሩ ለጥናት ቡድኑ መረጃ መስጠታቸውን ገልጸዋል።

ህወሓት በማይካድራ ዘርን መሰረት ያደረገ አንድ ሺህ 644 ሰዎች ላይ ዘግናኝ ጭፍጨፋ በማድረግ የአንድ ሺህ 563 ሰዎች ህይወታቸውን በማጥፋት በጅምላ እንዲቀበሩ ማድረጉ የባህሪው ማሳያ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

# ‹‹ወደ ትግራይ የገባው...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አቶ ገብረፃድቅ ለወጋህታ ጋዜጣ እንደተናገሩት፣ የፌዴራል መንግሥት ሰብዓዊ እርዳታ ወደ ትግራይ እንዲደርስ ቆራጥ እርምጃ መውሰዱ የሚያስመሰግነው ነው። ወደ ትግራይ ክልል የሚሄደው ሰብዓዊ ዕርዳታ ህወሓት ወደ ተቸገረው ህዝብ በትክክል ማድረስ ይጠበቅበታል።

ከዚህ ቀደም ለትግራይ ህዝብ ተብሎ የገባውን ሰብዓዊ እርዳታ ሕወሓት ለተቸገረው ህዝብ ከመከፋፈል ይልቅ ታጣቂ ኃይሎቹን ይመግብበት እንደነበር አውስተው፤ከታጣቂ ሃይሎቹ የተረፈውን የዕርዳታ እህልና መድኃኒቶችም ለነጋዴዎች በመሸጥ ገንዘብ ለመሰብሰብ ይጠቀምበት እንደነበር አስገንዝበዋል።ከዚህ መነሻነትም ወደ ትግራይ ክልል እየገባ ያለው የሰብዓዊ እርዳታ ለተቸገረው ህዝብ በትክክል መድረሱንም ዓለም አቀፍ ተቋማት ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል ሲሉ አመልክተዋል።

ሕወሓት ለትግራይ ህዝብ የተላከውን ዕርዳታ ለታጣቂ ኃይሎቹ ይመግብበትና የተረፈውንም ለነጋዴዎች ይሸጠው እንደነበርም ከትግራይ ወደ አማራ ክልል ተፈናቅለው የመጡ ተጋሩዎችም ጭምር ምስክርነት የሰጡበት መሆኑን አስታውሰዋል።

ወደ ትግራይ ክልል የሚሄደውን የሰብዓዊ ዕርዳታ ትክክለኛ አሰጣጥ ስርአት እንደሌለ ያሳያል ያሉት አቶ ገብረፃድቅ፣ ለትግራይ ህዝብ የተላከ ሰብአዊ እርዳታ ከዓላማ ውጭ እንዲውል መደረጉ ሕወሓት ሰብዓዊነት የጎደለው አካሄድ እየተከተለ መሆኑ የሚያረጋግጥ ነው ብለዋል ።

የፌዴራል መንግሥት ሰብዓዊ እርዳታ ወደ ትግራይ ክልል እንዲላክ ያደረገው የተቸገረውን የትግራይ ህዝብ ለማገዝ እንጂ ህወሓት አለአግባብ እንዲጠቀምበት አይደለም ያሉት ኃላፊው፣ ወደ ክልሉ የገባ ሰብዓዊ እርዳታ ህዝቡ በትክክል እንዲደርሰው ሊከታተልና ሊታገል እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

የሰብዓዊ እርዳታ አቅራቢ ድርጅቶችም ወደ ትግራይ እየገባ ያለው እርዳታ በትክክል ወደ ተቸገረው ህዝብ እየተሰራጨ መሆኑን ሊከታተሉ እንደሚገባም አስታውቀዋል።

ህዝብ ከሚኖርበት አካባቢ ሳይፈናቀል ሰብዓዊ እርዳታ እንዲያገኝ መንግሥት አሁንም ቁርጠኛ መሆኑን አመልክተው፤ የዓለም መንግሥታትም ይህን ቁርጠኝነትና ውሳኔ በአወንታዊ መልክ እየተመለከቱት መሆኑን ተናግረዋል።

ሰብዓዊ እርዳታው ለተቸገረው ህዝብ በትክክል እየደረሰ ካልሆነ አሁንም የትግራይ ህዝብ ጠላት ህወሓት መሆኑን ያረጋግጣል ብለዋል።

የትግራይ ህዝብ የህወሓት ቡድን በፈጠረው ችግር በብዛት እየተፈናቀለ እንደሚገኝ ጠቅሰው፤ ይህ ሁኔታ በዚህ ከቀጠለ ለአገር ይሁን ለትግራይ ህዝብ ከባድ ቀውስ የሚፈጥር በመሆኑ መንግሥት ይህን ተገንዝቦ ህዝቡ ከቀዬው ሳይፈናቀል ሰብዓዊ እርዳታ እንዲያገኝ እየሰራ እንደሚገኝ ገልፀዋል።

የኢትዮጵያ መንግሥት ለትግራይ ህዝብ ሰብዓዊ እርዳታ አልከለከለም፤ መከላከያ ሠራዊት ከትግራይ ሲወጣም መንግሥት እህል፣ ነዳጅ ወዘተ ትቶ ነው የወጣው እንጂ ህወሓት እንደሚነዛው ፕሮፖጋዳ አይደለም። ብልፅግና ፓርቲ ለትግራይ ህዝብ እንዲጠቀም እንጂ እንዲጎዳ ፍላጎት የለውም ሲሉ አረጋግጠዋል።

መንግሥት በወሰደው ቆራጥ እርምጃ ተከትሎ ባለፉት ጥቂት ቀናት የእርዳታ እህል፣ የህክምና ቁሳቁሶች፣ መድኃኒቶችና ነዳጅ የጫኑ ተሽከርካሪዎች አብአላ አድርገው እየገቡ መሆኑን የዓለም አቀፉ ቀይ መስቀል ድርጅትና ሌሎች ዓለም አቀፍ ተቋማትና አገራት ምስክርነት መስጠታቸው ይታወቃል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የሰብዓዊ መብት ተቋማት ሥራ ሰብዓዊነት እንጂ የፖለቲካ ፍላጎት አስፈጻሚነት ሊሆን አይገባም!

የሰብዓዊ መብትን እና የዴሞክራሲ ጉዳዮችን ማዕከል አድርገው የሚንቀሳቀሱ እንደ አምነስቲ ኢንተርናሽናል እና ሂውማን ራይትስዎችን የመሳሰሉ በርካታ ተቋማት፤ የመመስረታቸውን ዓላማ ለተመለከተው ለሰው ልጆች ሰብዓዊ መብት መከበርና ለዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ እውን መሆን በሰውነት ሚዛን ላይ ሆኖ ያለልዩነት ለሁሉም የሰው ልጆች መሟገት እንደሆነ ይረዳል፡፡ ይሄን አይነት የተቀደሰ ዓላማን የያዘ አንድ ተቋም ደግሞ ለዓላማው መሳካት ከየትኛውም የፖለቲካም ሆነ የሌላ አጀንዳ ተሸካሚነት ራሱን ማራቅ፤ ጉዳዩም ፖለቲካ ሳይሆን ሰብዓዊነት ሊሆን የተገባ ነው፡፡

የዘመናችን አምነስቲ ኢንተርናሽናል እና መሰሎቹ ግን የሰብዓዊ መብትና ዴሞክራሲን ለምድን ደርበው የተፈለፈሉበትን ንፍቀ ዓለም ጥቅምና ፍላጎት የማስፈጸሚያ ሁነኛ መሳሪያ ሆነው መፈጠራቸው የአደባባይ ምስጢር ሆኗል፡፡ እነዚህ ተቋማት ከጊዜ ወደ ጊዜ ዓላማቸው ፖለቲካን ማስፈጸም፣ ሂደታቸው ከፋፋይነት፣ ግባቸው እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ብሩህ ተስፋ ያላቸው አገራትን ጉዞ ማጨናገፍ መሆኑ እየተገለጠ መጥቷል፡፡

ለዚህ ሂደታቸው መሳካት የደረቡት የሰብዓዊነትን ካባ ሁነኛ መሳሪያ ሆኗቸዋል፡፡ እናም ለምዕራቡ ዓለም ምቹ የሆኑ አገራትን በሰጥቶ መቀበል መርህ ብዙ ፖለቲካዊ ትርፍ አግኝተው ጥቂት የጥገኝነት አጎልባች ሰብዓዊነት ድጋፍ ያደርሳሉ፡፡ በተቃራኒው ለምዕራቡ ዓለም ክብሬንና ጥቅሜን አሳልፌ አልሰጥም ያለ አገር ሲኖር በሰብዓዊነት ስም በዘረጉት መዋቅር ተጠቅመው የዛን አገር ገጽታ ማጠልሸት፣ ፖለቲካውን ማደፍረስ፣ የሕዝቦችን አንድነት መሸርሸርና አገር የማዳከም ተልዕኳቸውን ለማሳካት ይታትራሉ፡፡

በኢትዮጵያ የሆነውና እየሆነ ያለውም ይሄው ነው፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ተቋማት በዘመነ ሕወሓት/ኢህአዴግ በኢትዮጵያ አያሌ ዜጎች ለከፋ ጭቆናና ሰብዓዊ ጥቃት ሲዳረጉ አልተነፈሱም፤ በኢትዮጵያም ሆነ በሥርዓቱ ላይ ሪፖርት አላቀናበሩም፤ በኢትዮጵያ ላይ ለሚጣል ማዕቀብና እጅ ለሚጠመዝዝ ሕግ ግብዓት የሚሆን የተጠናቀረ ሪፖርትም አላቀረቡም፡፡ ምክንያቱም ዘመኑ እነሱ ብዙ አትርፈው ጥቂት ዳረጎት የሚያበረክቱበት ነበርና ነው፡፡

ዛሬ ላይ ግን እነዲነካባቸው የማይፈልጉት አሸባሪው ሕወሓት ህልውናው አደጋ ላይ ሲወድቅ ግን ታሪክ ተቀየረ፤ ኢትዮጵያን ማጠልሸት፣ በሕዝቦች መካከል መከፋፈልን የሚፈጥሩ ዘገባዎች እንዲሰሩ ግብዓት ማቀበል፤ ኢትዮጵያውያንን እርስበእርስ የሚያባላ የመሰላቸውን የተቀነባበረ "የዘር ማጽዳት" የሚል የዳቦ ስም የሰጡትን ሪፖርት ባናት ባናቱ ማከታተል፤ ይሄን መነሻ በማድረግም የምዕራቡ ዓለም (በተለይ አሜሪካና ሸሪኮቿ) በኢትዮጵያ ላይ ማዕቀብና እጅ ጠምዛዥ ሕጎች እንዲያዘጋጁና ተግባራዊ እንዲያደርግ መጎትጎት ዋና ሥራቸው ሆነ፡፡

አምነስቲ እና መሰሎቹ፣ በሕወሓት/ኢህአዴግ የ27 ዓመታት የግፍ አገዛዝ ጉዞ ስለ ሕዝብ ያልተከፈተ አንደበታቸው፤ ስለ ንጹሃን ያልተከተበ ብዕራቸው፤ ባለፉት ሦስት ዓመታት ስለሕወሓት ሕልውና ሲሉ አንደበታቸው ሃሰትን፣ ብዕራቸው ቅጥፈትን በማቀበል ተጠመዱ፡፡ ከሰሞኑ አምስቲ ኢንተርናሽናል እና ሂውማን ራይትስ ዎች የተባሉት እነዚሁ ተቋማት በወልቃይትና አካባቢው ላይ አተኩረው ያወጡት ሪፖርት የዚሁ ከሰብዓዊነት የራቀ የፖለቲካ ፍላጎት አስፈጻሚነታቸውን ገሃድ ያወጣ ተግባር ነው፡፡

ምክንያቱም አካባቢው በዘመነ ሕወሓት የከፋ ግፍና ዘር ተኮር ጭፍጨፋ የተደረገበት ለመሆኑ በርካቶች ሲናገሩ ቆይተዋል፡፡ ከሰሞኑም የጎንደር ዩኒቨርሲቲ የጥናት ቡድን ይፋ ያደረገው ይሄንኑ የ40 ዓመታት የግፍና ጭቆና እውነት ነው፡፡ ይሁን እንጂ አምነስቲ እና ሂውማን ራይትስ ዎች ከትናንት በስቲያ ያቀረቡት ሪፖርት ይሄንን ሃቅ ያልተመለከተ ይልቁንም ባለፉት ሶስት ዓመታት ተፈጸሙ ያላቿውን ጉዳዮች ብቻ ለፖለቲካ ተልዕኳቸው በሚያመች መልኩ ያጠናቀሩት ነበር፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ተቋማት ውግንናቸው ለሰው ልጅ፤ ግባቸው ዴሞክራሲ ማስፈን ቢሆን ኖሮ በወልቃይትና ሁመራ አካባቢዎች ቀደም ሲል በሕወሓት ሲፈጸሙ የነበሩ ግፍና ሰቆቃዎችን ለመመልከት አይናቸው ባልተጋረደ፤ ልቦናቸውም ባልተደፈነ ነበር፡፡

ይሄንን ሪፖርት ሲያዘጋጁም ሰብዓዊነትን ሳይሆን ፖለቲካዊ ሸፍጥን አንግበው ነው፡፡ ዓላማቸውም በኢትዮጵያውያን መካከል ቂምና ቁርሾን መፍጠር፣ በኢትዮጵያ ላይ ደግሞ ጫናን ማሳደርና የመንግሥትን ቅቡልነት ማዳከም ከመሆኑ ባሻገር፤ በኢትዮጵያ ላይ የምዕራቡን ዓለም ጥቅምና ፍላጎት ለማስፈጸም የሚያስችሉ እንደ ኤች አር 6600 እና ኤስ 3199 ለመሳሰሉ እጅ ጠምዛዥ ሕጎች ግብዓትነት ማዋል ነው፡፡ ይህ አይነት አካሄድ ደግሞ ተቋማቱ የተሰማሩበትን ዓላማ እንዲስቱ ከማድረጉም በላይ፤ በኢትዮጵያውያን ዘንድም ተቀባይነት የሌለው የመርጦ አልቃሽነት ዜማ ተደርጎ የሚወሰድ፤ የሰብዓዊ መብት ተቋማት ሥራም ሰብዓዊነት እንጂ የፖለቲካ ፍላጎት አስፈጻሚነት አለመሆኑን ለማስገንዘብ እንዲነሱ ያደረገ ነው!


እናፕድ

## አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

# ኢትዮጵያ ትጣራለች

**ታምራት ተስፋዬ**

የኢትዮጵያዊነት ትርጉም ፍቺ ቅኔና ወርቁ ረቂቅ ነው። ኢትዮጵያውያንም አገራቸውን የሚወዱ፣ አገራቸው ተሻሽላና አድጋ ማየት የሚፈልጉ፣ ይህንንም ከልብ የሚመኙና ለዚያም የሚታገሉ ናቸው። ይህ ማለት ግን በዘርና በጎሳ ልክፍት የተለከፉ ጸረ ኢትዮጵያና ጸረ ኢትዮጵያዊነት አቋም ያላቸው የሉም ማለት አይደለም፤ እንዳሉ አይካድም።

ይሁንና «ነብር ዥንጉርጉርነቱን ኢትዮጵያዊም ኢትዮጵያዊነቱን አይተውም እንደሚባለው» እውነተኛ ኢትዮጵያውያንም መቼም ቢሆን ለአገራቸው ያላቸው ፍቅርና አክብሮት የሚለወጥ አይደለም። እድገቷን እንጂ ዝቅታዋን፣ ደስታዋን እንጂ ኀዘኗን፣ ክብሯን እንጂ ውርደቷን ፈጽሞ የሚመኙም አይደሉም።

ኢትዮጵያውያን ለአገራቸው ያላቸው ፍቅር በቃላት ብቻ የማይገለጽ ስለመሆኑ የቀደሙ ታሪኮችም ሆኑ የእስካሁን ክንዋኔዎች ምስክር ናቸው። ኢትዮጵያውያንም የአገራችን ጉዳይ ሲነሣ ደመ ቁጡዎች፣ አትንኩን ባዮችና ኮስታሮች መሆናቸው የአደባባይ ሃቅ ነው።

አገሩ ሲደፈር «እንዴት ተደርጎ» የማይል ኢትዮጵያዊ ይኖራል ተብሎም ፈጽሞ አይታሰብም። ኢትዮጵያውያንም አገራቸውን የነኩባቸው እለት ትንታግና አይነኬ አራስ ነብር እንደሚመስሉ፣ በአገራቸው ለመጣ ሞትን እንደ ሰርግ እንደሚቆጥሩም የሩቅ ሳይሆን የቅርብ ሁነቶች በቂ ምስክር ናቸው።

በየዘመናቱ የተነሱ ጠላቶቿን በሕዝቦቿ አንድነትና የጋራ ክንድ እያሳፈረች ዘመናትን የተሻገረችውና ለጥቁሮች የነፃነት ምልክት የሆነችው ኢትዮጵያም እንደ ትናንቱ ሁሉ ዛሬም ቢሆን ግን ጠላቶቿ አላንቀላፉም። በውስጥም ሆነ በውጭ የሚገኙ ጠላቶቿ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊና መስተጋብሯን ለማናጋት ረጃጅም እጆቻቸውን ዘርግተውባታል።

አንዳንዶቹም ሉዓላዊነቷን በመዳፈር ነፍስ እንዳላወቀ ሕፃን ልጅ በሞግዚት አስተዳደር የማስተዳደርና የመጠበቅ ህልማቸውን ለማሳካት ማእቀብ ከማወጅ፣ ረቂቅ ሕግ ከመቀመር አንስቶ በየጊዜው ሴራቸውን እየቀያየሩ መከሰት ተይይዘውታል።

እንደ ትናንቱ ሁሉ የኢትዮጵያ ወቅታዊ ፈተና እንዲቀል የሁላችንም አበርክቶ የግድ ይላል። ወቅቱም የኢትዮጵያን ችግሮች የመሸሸ ሳይሆን የማሸሸ ተጋድሎን ይጠይቃል። ኢትዮጵያም በአገራዊ የአንድነት አስተሳሰብና የፍቅር ውል ኪዳን የተሳሰሩና የታነጹ ልጆቿን ከመቼውም ጊዜ በላይ ትሻለች።፡

በእርግጥ «ማን ነው ኢትዮጵያን አገሩን የሚወድ? እጁን ያውጣ» ቢባል ሁሉም እጁን ያወጣል። «ኢትዮጵያ ሰላም እንድትሆን የሚፈልግስ?» ተብሎ ቢጠየቅ፤ አሁንም ሁሉም የአገሩን ሰላም እንደሚፈልግ ይናገራል። አበው «ያሉት ከሚጠፉ የወለዱት ይጥፉ" ይሉናል። ይህንን የሚሉን «ቃል» ምን ያህል ከባድ እንደሆነና፤ ከወለዱትም ልጅ በላይ ሊጠብቁት የሚገባ መሆኑን ሲያስገነዝቡን ነው።

«አገሬን እወዳለሁ» ስንል ግን የእለት ተእለት ተግባራችንም ይህንኑ ቃላችን የሚያስታውስና የሚያስመ ሰክር ሊሆን ይገባዋል። አገሩን የሚወድ በአገሩ ጉዳይ ዳር ተመልካች አይሆንም። አገሩን የሚወድ የአገሩን ጥቅም ያስከብራል፡፡

አገሩን የሚወድ ለአገሩ ዘብ ይቆማል። አገሩን የሚወድ ፍላጎቱን ከአገሩ ፍላጎት አያስበልጥም። በአጠቃላይ አገሩን የሚወድ ማንኛውም ዜጋ ከምንም ነገር በላይ ቅድሚያ መስጠት ያለበት ለአገሩ ህልውና መሆኑ የሚያከርክር አይደለም።

በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ከመቼውም ጊዜ በላይ በአንድነት በመቆም ሰንደቋን ከፍ አድርገው ወደ ታላቅነት ክብሯ የሚመልሱ አገር ወዳድ ልጆች ያስፈልጋታል። የጠላቶቿን ዓላማ ለማምከን ጀርባቸውን ሳይሆን ግንባራቸውን የሚሰጡ ልጆችን ትሻለች።

አሁን ላይ እናት አገር ኢትዮጵያ እየተጣራች ነው። እድገቷም ውድቀቷም በእኛ በልጆቿ እጅ ላይ ነውና አቤት አለሁልሽ እንበላት። ለኢትዮጵያ ያለናት እኛው ነን። ለእኛም ያለችን እሷ ናት። ስንኖርላት ታኖረናለች። ስንዋደቅላት ታቆመናለች። ስንበረታላት ትበረታለች። ትጠነክራለች።

አሁን ላይ እናት አገር ኢትዮጵያ እየተጣራች ነው። ነገዋን ማሳመር የምንችለው ልጆቿ ብቻ ነንና አቤት እንበላት። ምሬቷን በሀሴት እንቀይርላት። መከፋቷን በደስታ እንለውጥላት። ዝቅታዋን ለሚመኙ ከፍታዋን እናሳይላት። ወዛን ከሚነጥቁ ውበቷንም ከሚሰርቁ እንታደጋት።

ኢትዮጵያ አይናችን ናት። አይናችንን አናስደፍር። በአይን አይቀለድም። ኢትዮጵያ የምትፈልገን ትክክለኛ ጊዜ ላይ ነን። አስተማማኝ ምርኩዝ እንሁናት። ኢትዮጵያ ካለ እኔና እናንተ አትበረታም። በነጻነት መቆም ከፈለግን በያለንበት ኢትዮጵያን አንጣላት። በኢትዮጵያ ለመጣ ምንም ነገር ወደ ኋላ አንበል። በክብሯ ሲመጡ በስብዕናችን እንደመጡ እናስብ። እርሷን የነካ አይናችንን እንደነካ እንወቅ።

ኢትዮጵያ ወድቃ እኛ እንደማንቆም፣ እኛ የምንከበረው በእሷ ተከብሮ መቆየት ውስጥ መሆኑን፣ እሷ ጎድሎባት እኛ እንደማይሞላልን፣ እሷ ዝቅ ብላ እኛ እንደማንገዝፍ፣ እሷ እያዘነች እኛ እንደማንደሰት፣ እሷን ረስተን እኛ እንደማንታወስ፣ ጠንቅቀን መገንዘብ ይኖርብናል።

ዛሬ ላይ የደረስነው በአገራችን አትምጡብን ብለን በአንድነት በተፋለምነው እልህ አስጨራሽ ትግል ውጤት ነው። ትናንት ግን ዛሬ አይደለም። ወቅቱም በትናንት ተጋድሎ ተኩራርተን ሩጫችንን የምንገታበት አይደለም። ይልቁንስ የቅብብሎሽ ሩጫችንን ለማፍጠን ተጨማሪ ጥረት ግድ የሚልበት ነው። እዚህ ላይ ሩጫን ማቋረጥ ለተሸናፊነት ይዳርጋል።

እናም ትንሽዋ ተግባር ወይም ትንሽዋ የእሳት ፍም እንኳ የራሷን ተጽእኖ ታሳርፋለችና በጀመረነው ትንፋሽ የማይሰጥ ሩጫ ሌሎችን በረጅም ርቀት ለመቅደም ፈጣን የአሯሯጥ ማስተካከያ ማድረግ ይኖርብናል። በዚህ አገርን የመጠበቅ ተጋድሎም «ከእኔ የሚጠይቀውን ሁሉ ለማድረግ እጓጓለሁ፤ ዝግጁም ነኝ» የሚል ዜጋ የግድ ይላል።

ከፍታችንን ለማዝለቅ የነበርንበትን የኋሊት እያስታወስን፣ ከምናደንቀው ተምረን የቆሞ ቀርነት ታሪካችንንም አውግዘን በሌላ አነጋገር ከስኬታችንም ከጉድለታችንም እውቀት ቀስመን ወደፊት መሮጥ ይኖርብናል። ይህን ፍልሚያ አሸንፎ መውጣት ካለብን ጅማሪያችን እንዲህ ካሉ ተግባራት መሆን ይገባዋል። የምንፈልጋትን ኢትዮጵያ መገንባት የምንችለው ይህም ሲሆን ነው ።

ከፊታችን እጅግ ብዙ ሥራዎች ይጠብቁናል። ዛሬ ላይ በጋራ የፈነጠቀናትን የእድገት ጭላንጭል ወደ ተንቀጠቀጠ ደመራ ለማሸጋገር እልህ አስጨራሽ ትግሉ ከፊታችን ተደቅኗል። ፍልሚያ በድል መወጣት ካለብን ደግሞ ቆሞ ቀርነት ማስወገድ የግድ ይላል።

ዓለም ላይ ጣፋጩን ስኬት የሚያጣጥሙም የሚጀምሩ ሳይሆኑ የሚጨርሱ ናቸው። መጀመርም ይልቅ መጨረስ ትጋት ይጠይቃል። በመጀመራችን ብቻ ሳይሆን ስለመጨረሳችንም እርግጠኞች ልንሆን ይገባል። ኢትዮጵያን የማስከበሩ ተጋድሎ በፍፃሜ እንጂ በጅማሬ ብቻ አይመጣም።

ፈለግንም አልፈለግን በወቅታዊው ፈተና መፈተናችን አይቀርም። ይሁንና ቆሞ ከመሞት እየዳሁ መኖር ያዋጣል። እናም በምንም ዓይነት አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ብንሆንም የሚበጀንን በውል እየለየን የጀመርነውን የህልውና ጉዞ መቀጠል ይኖርብናል።

ፈተናዎቻችን የጥንካሬአችን ማሳያ ማድረግ ይኖርብናል። ከፈተናችን መጠንከር ይልቅ የእምነታችን መላላት በቁም ይጨርሰናል። ማመን ያለብን አንድ እውነት ቢኖር የጠላት ክንድ መቼም አያሸንፈንም። ብንወድቅም እየተነሳን ብንሞትም እየተተካካን አገራችንን ማስቀጠል የግድ ይለናል።

በተራመድን ቁጥር የአገራችን ክብር የምናስቀጥል በመሆኑ በፍፁም ለሚያቆሙን መቆም የለብንም። መንቀሳቀስ ለምንፈልገው ነገር ቅርብ ያደርገናልና ተራምደን ለመድረስ እንጂ ቆመን ለማልቀስ እጅ አንስጥ። በማይቆም ጥረት ውስጥ ስንኖር ደግሞ ለማይቀር ድል እንታጫለን።

«What Goes Around Comes Around» እንደሚባለው፣ የምናጭደውም ከዘራነው ውጪ አይሆንም። ሽንፈታችን የሚፀናው ፍልሚያ ለማቆም ስንቆም ነው። ድላችን ሁሉ ትግላችንን መሰረት ያደርጋል። ስኬታችንም የጽናታችን ውጤት ነው።

ለብሔራዊ ጥቅም መከበር በተለይም በ no more ም ሆነ ኤች አር 6600 እንዲሁም ኤስ 3199 የተሰኙ ረቂቅ ሕጎችን እንዳይፀድቁ ለማድረግ ያስመለከትነውና እያስመለከትን የምንገኘውን ተጋድሎ በማስቀጠል ነገ ቀና ብለን ለመኖር ዛሬ ላይ ኢትዮጵያን ከሚያስጎነብሷት እንጠብቃት። ይህን ስናደርግ ኢትዮጵያን የተበተቡ ሰንሰለቶች ይበጣጠሳሉ። የተቆለለባት የሴራ ተራራ ይናዳል። የጨለማውን ዘመን አልፋ ብርሃን በእናት አገራቸው ጸዳል ላይ ያበራል።

በጽናታችን ከጸናን ውጤት አይርቀንም። በየሚሆነው ሁሉ ያንገዳግደን ይሆን እንጂ አይጥለንም። ባለመሰልቸት ከታገልን የፈለግነውን ከማግኘት የሚያቆመን ሃይል አይኖርም። አገራችን ኢትዮጵያን አቤት እንበላት። አቤት አለሁልሽ ስንላት ጠላቶቿን ሁሉ ታሸንፋለች። ዳግምም ታብባለች።

# የለውጥ ጉዞው በሃሳብ ልዕልና፣ የአገር ግንባታውም በመግባባት ይሁን

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ዓለም በሁለት ጥንድ አስተሳሰብ ስር የወደቀች ይመስለኛል፤ ለምሳሌ፣ አገር በአንድ አይነት ሀሳብ ብቻ የሚገነባ የሚመስላቸው እና የተለያዩ ሀሳቦችን ወደ አንድ በማምጣት አገር መገንባት የሚቻል በሚመስላቸው ሰዎች። ርዕይ ያላቸውና አገር ለማቆም የሚተጉ ልቦች አገር በተለያዩ ሀሳቦች ነገር ግን በአስታራቂ እውነት እንደምትገነባ የሚያምኑ ሲሆን፤ በተቃራኒው እንደ እኛ አይነት ከመግባባት ይልቅ በተቃርኖ ሀሳብ ጦር መማዘዝን ባህል ያደረጉ አገራት ለምንም ነገር አንድ አይነትነትን የሚያስቀድሙ ናቸው። ይሁን እንጂ ዓለም አንድ አይነት የሆነ ምንም ነገር የላትም። ከትላንት እስከዛሬ በመለያየትና በተቃርኖ ነገር ግን በአስታራቂ ሀሳብ የቆመች ናት። ለምንም ነገር አንድ አይነት መሆንን የሚመርጡ ግለሰቦች ገና የዘመናዊውን ዓለም ሰፊ ምህዳር ያልዳሰሱ ናቸው ብዬ በግልጽ መናገር እችላለሁ። በእንዲህ አይነት አስተሳሰብ ስር የወደቁ አገራት አይደለም ትውልድ፣ አይደለም አገርና ሕዝብ ቀርቶ ራሳቸውን እንኳን ከራሳቸው ጋር ማግባባት አይችሉም።

አገር የተለያየ ሀሳብ ነው የሚያስፈልጋት። የአሁኑ ስልጣኔና እርምጃ የመጣው በተለያዩ ሰዎች የተለያየ ሀሳብ ነው። ሀሳባችን ሌሎችን እስካልጎዳ ድረስ የተለየ መሆኑ ያን ያክል ችግር ይኖረዋል ብዬ ባላስብም በመነጋገርና በመወያየት ሁሉንም ወደሚያስማማ እውነት መጠጋት ግን የበለጠ አዋጭ እንደሆነ አምናለሁ። የትኛውም አገርና ሕዝብ በተመሳሳይ ባህልና ሥርዓት፣ ወግና ልማድ፣ አስተሳሰብና ርዕዮተ ዓለም አልቆምም። አገራችን ኢትዮጵያ የብሔር ብሔረሰብ ጉራማይሌ መልክ ናት፤ ከነዚህ በርካታ ብሔረሰቦች መካከል የሚወጣው የሀሳብ መልክ ደግሞ የተለያየ ነው። እኚህ የተለያዩ የብሄር ሀሳቦች ለኢትዮጵያ ተጨማሪ ውበት እንጂ ተጨማሪ ስቃይ እንዲሆኑ መፍቀድ የለብንም። እኛ ከተግባባን፣ ፖለቲከኞቻችን ለመስማማት ከተዘጋጁ ወደ ጦርነት የሚወስድ ሀሳብ ይኖረናል ብዬ አላስብም። ሁሉም ሀሳቦች ምንም ያክል ቢጎረብጡም በንግግር የሚታረቁ ናቸው። ሆኖም ለአመታት እኔ ብቻ ነኝ ልክ በሚል አጉል አመለካከት ተተብትበን አገራችንን ላልተገባ ስቃይ ስንዳርጋት ኖረናል፤ አሁን ግን ጊዜው ለዚህ የሚሆን አይደለም፤ በመነጋገር መስማማት ይኖርብናል።

ብዙዎች በመነጋገር ከኋላችን ተነስተው ጥለውን እየሄዱ ነው፤ ብዙ አገራት በእኛ መፈጠር ተፈጥረው እኛን ለማሸማገል መሀላችን ሲገቡ እያየን ነው፤ ይሄ ለእኛ አይመጥነንም። ይሄ ለታላቋ ኢትዮጵያ አይገባም። በእርቅና በመግባባት የጥንቱን ታላቅነታችንን መመለስ ይኖርብናል። ለብዙ የዓለም አገራት፣ ለብዙ የአፍሪካ አገራት ለሰላም ግንባታ ሰራዊቶቿን እየላከች ሰላም ስታሰፍን የቆየች አገር ዛሬ ሰላም ርቋት ስትታይ ያሳዝናል። ምስራቅ አፍሪካ እኮ ኢትዮጵያን ተደግፉ ነው የቆመችው። የአፍሪካ እናት እኮ ኢትዮጵያ ናት፤ ችግሮቻችንን በሀሳብ የበላይነት በማሸነፍ ስማችንን ማደስ ከሁላችንም የሚጠበቅ ጉዳይ ነው። ህንድ በሕዝብ ብዛት ከዓለም ሁለተኛ ናት፤ በውስጧም ከሁለት ሺህ በላይ ቋንቋዎች ይነገሩባታል፤ ላለፉት እጅግ በርካታ አመታት ምንም አይነት ጦርነት ተስተናግዶባት አያውቅም። ናይጄሪያ በሕዝብ ብዛት ከአፍሪካ ቀዳሚ ከዓለምም ከቀዳሚዎቹ ተርታ ናት፤ በውስጧም ከአምስት መቶ በላይ የተለያዩ ጎሳዎች ይኖራሉ፤ የሕዝብ ብዛቷና የጎሳዋ መብዛት ግን ችግር አልፈጠረባትም። መነጋገርን ያስቀደመ ማህበረሰብ ልዩነቶቹ ምንም ያክል ቢጎሉም ኢምንት ናቸው።

ነገሮች በእኛ አስተሳሰብ ስር ናቸው፤ አስተሳሰባችንን መቆጣጠርና መግራት ካልቻልን ለነገሮች ባሪያና አልሸነፍ ባይነትን ነው የምንለምደው። በሀሳባቸው ተፅዕኖ ስር የወደቁ ሰዎች ተነጋግሮ መግባባት አይቻላቸውም። አይደለም ከሌላው ጋር ከራሳቸው ጋርም መግባባት አይቻላቸውም። የአገራችን አብዛኛው ችግር ይሄ ነው፤ ለሀሳቦቻችን ቅድሚያ የሰጠን ነን። ምንም ያክል አዋጪና በላጭ አስተያየት ብንሰማ እንኳን እኔ ያልኩት ካልሆነ የምንል አይነት ነን። እኚህ አስተሳሰቦች ናቸው ዛሬ ላይ ዋጋ እያስከፈሉን የሚገኙት። አገራችን በላጭ ሀሳብ ያስፈልጋታል። በበላጭ ሀሳብ አገራችንን መምራት ልምድ ማድረግ ይኖርብናል። በላጭ ሀሳብ በሌለበትና ተነጋግሮ መግባባት በማይችል አገርና ሕዝብ ውስጥ ነውጥ እንጂ ለውጥ የለም። መገፋፋት እንጂ መተቃቀፍ አይታሰብም። መነጋገር እኮ ዘመናዊነት ነው፤ ዘመናዊነትን መዝገበ ቃል ላይ ብትፈልጉት፣ ከብዙ ዝርዝሮች ውስጥ ተነጋግሮ መግባባት የሚል መልስ ይሰጣችኋል።



> አብዛኞቹ ችግሮች
> ትላንት ወለድ ናቸው።
> በታሪክ የምንጣላ ብዙዎች ነን።
> ባልኖርንበትና በማናውቀው ትላንትና
> ውስጥ ገብተን በሰማንውና ባደመጥነው
> በጥቂት ግለሰቦች የውሸት ትርክት
> አይጥና ድመት የሆንን ብዙ ነን።
> ሰው እንዴት በማያውቀው
> ትላንት ይጣላል? የሆነው ሆኖ
> ላጣሉንም..እያጣሉን ላሉ ነገሮችም
> በመነጋገር ሰላም እናውርድ።
> ከሌላው ጋር ለመግባባት
> መጀመሪያ ከራሳችን ጋር
> መግባባት ይኖርብናል።
> ከራሱ ጋር የተግባባ ከሌላው ጋር
> ለመግባባት አይቸግረውም።

እንደ ዜጋ ዘመናዊነታችንን ተነጋግሮ በመግባባት ውስጥ ልንፈልገው ይገባል። እንደ አገር ዘመናዊነታችንን በውይይት መጀመር ይኖርብናል። ባለመነጋገር ከዘመናዊነት ርቀን የሰነበትንባቸው እነዛ በርካታ ዓመታት አስተምረውናል ብዬ አስባለሁ። ባለመነጋገር ሰላማችንን፣ አንድነታችንን ነጥቀውን አለያይተውን ነበር። አሁን ግን መከራ ይበቃናል፤ በጠብመንጃ ሳይሆን በውይይት፣ በመለያየት ሳይሆን በመቀራረብ ሰላም ማምጣት መልመድ ይኖርብናል። የዓለም ስልጣኔ በመነጋገር ውስጥ የቆመ ነው። ወደ አፍሪካ ስንመጣ ግን ይሄ እውነት ጎልቶ አይታይም። በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚው፣ በማህበራዊ ሕይወታችን ባጠቃላይ በእያንዳንዱ የሕይወት እንቅስቃሴያችን ላይ የውይይት ስልጣኔ አይስተዋልም። ለብዙ ነገር ሰልተን ለመነጋገር ሲሆን ግን የከሸፍን ነን። አፍሪካን ዋጋ እያስከፈላት ካለው ነገር ውስጥ አንዱና ዋነኛው ይሄ ነው ብዬ አስባለሁ። ወደ እኛ አገር ስንመጣ ደግሞ የከፋ ሆኖ እናገኘዋለን። ያለፉት ሃምሳ አመታት ካለመነጋገር ጦርና ጎራዴ የተማዘዝንባቸው ሆነው ያለፉ ነበሩ። በቀላል ነገር ብዙ ነገሮችን ያጣንባቸው ጊዜያቶች ነበሩ።

እንደ አያቴ ጥበበኛ ሴት አላውቅም፤ በሕይወቴ ሁሉ የምታስገርመኝ ሴት ናት። ምድር ላይ ዘጠና ስድስት አመት ስትኖር ሁሌ የምትለው አንድ ነገር ነበር "መተው ነገሬን ከተተው..» እንደ አያቴ የመተውን ጥበብ ያስተማረኝ ማንም የለም። በአያቴ ነፍስ ውስጥ፣ በአያቴ ሴትነት ውስጥ በእርጅናዋ ውስጥ ሳይቀር አፍርቶና ጎምርቶ ያገኘሁት አንድ ታላቅ ጥበብ ቢኖር የመተው ጥበብ ነው። የአያቴ እውነት ይሄ ብቻ አይደለም እውነተኛ አሸናፊነት የት እንዳለ የምታውቅ ሴት ነበረች። እውነተኛ አሸናፊነት በመተውና በመቻል ውስጥ ነው ያለው ብላኛለች። በትዕግስትና በይቅርታ ውስጥ ነው ያለው ብላ ነግራኝ ታውቃለች። ይሄንንም እውነት ስታስረግጥልኝ "መቻል ምን ይከፋል ሆድ ካገር ይሰፋል፤" ስትል አውግታኛለች። እኔና እናንተ ይሄን እውነት አናውቀውም። አያቴ ይቺን ምድር እስከተሰናበተችበት ጊዜ ድረስ በመተው ጥበቧ ለዘጠና ስድስት አመታት ከሰው ልጅ ሁሉ ጋር በመስማማት ኖራለች። የአያቴ እውነት.. እምነት ያስደንቀኛል። የጠፋችውን ኢትዮጵያ በእሷ ነፍስ ውስጥ፣ በእሷ ሴትነት ውስጥ አያታለሁ። የአያቴ እውነት አሁን ላለነው ለእኛ መልካም እውቀት ሆኖ ስላገኘሁት አካፈልኳችሁ።

አሁን ላለችው ኢትዮጵያ የአያቴ ጥበብ ያስፈልጋታል። አሁን ላለነው ትውልዶች የአያቴ እውነት ያስፈልገናል። አያቴ በመተው ውስጥ ከዘጠኝ አስርት አመታት በላይ በኩራትና በልዕልና ተራምዳለች። ሁላችንም ወደ መተው እንመለስ። ወደ ሆደ ሰፊነት፣ ወደ ሰምቶ መቻል እንመለስ። በትዕግስት፣ በይቅርታ ወደማሸነፍ እንሸጋገር። በውይይት ወደመርታት እንምጣ። ሳንግባባ የምንሄድባቸው መንገዶች ሩቅ አያደርሱንም። ሳንስማማ በልዩነት የምንራመድባቸው ጎዳናዎች አይባርኩንም። የምንመኛትን ኢትዮጵያ አንደርስባትም። ልንፈጥረው የምናስበውን ትውልድ አንታደገውም። ብንሄድ ብንሄድ ወደ ረፍታችን አንደርስም። የትንሳኤአችንን ጥጉን አናገኘውም። በመሆኑም ላሰብናቸው አገራዊ በጎ ሀሳቦች ሰላም ያስፈልገናል። አገራዊ መግባባት ግድ ይለናል። ሀሳቦቻችንን ካልገታናቸው ወይም ደግሞ በሌላ አስታራቂ እውነት ካልቀየርናቸው አደገኛ ነው የሚሆኑብን። ብዙ አገራት የፈረሱት፣ ብዙ ትውልዶች የመከኑት በሀሳብ ነው። እንደዚሁም ደግሞ በጋራና በመተማመን ሀሳብ ያተረፉ በርካታ አገራት አሉ። ለእኛም የሚያስፈልገን በጋራ ሀሳብ ወደፊት መሄድ ነው።

አገራችን በአሁኑ ሰዓት ወደ ከፍታ እርምጃ ላይ ናት፤ እርምጃዋ ይፈጥን ዘንድ ሁሉን አቀፍ ምክክር ያስፈልጋታል። ትላንት ላይ ለጦርነት ምክንያት የሆኑ የመለያየት ሀሳቦች በውይይት መፈታት ለአገራችን እርምጃ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው። ከታች እስከላይ ባለው አገራዊ መዋቅር ለነውጥና ለሰላም መደፍረስ መንስኤ የሚሆኑ ጉዳዮች እየተለዩ እልባት ቢሰጥባቸው እጅግ ዋጋ ያለው ነገር ነው። የውስጥና የውጭ ፖለቲካዊም ሆኑ ማህበራዊ ችግሮቻችን በጋራ ውይይት የሰላም ፀሀይ ቢወጣባቸው በብዙ እናተርፋለን ባይ ነኝ። እኛ እየኖርን ያለነው በድሮ ባህል ነው፤ ትላንትና ለጦርነት መንስኤ የሆኑ ችግሮቻችንን ዛሬም ለጦርነት እየተጠቀምንባቸው እንገኛለን። ተወያይቶ ከመስማማት ይልቅ ጎራ ወደመፍጠር መሄድ ይቀናናል። ትላንትናዎቻችን በዚህ ደረጃ የተቃኙ ነበሩ፤ እናም ልምዶቻችንን መቀየር ይኖርብናል። ዋጋ ያስከፈሉንን ትላንትናዎች ዛሬ ላይ መድገም አይኖርብንም። ኢትዮጵያ በለውጥ ጎዳና ላይ ናት ብለን ስንናገር በምክንያት መሆን አለበት። ምክንያቱም ለውጥ ብዙ ገጾች አሉት፤ የሁሉም ገጾች ማረፊያ ግን የሀሳብ የበላይነት ነው። የሀሳብ የበላይነት ደግሞ ተነጋግሮ በመስማማት የሚመጣ የስልጣኔ ከፍታ ነው። ለውጥ በሀሳብ የበላይነት ካልመጣ ጥያቄ ውስጥ ይወድቃል።

ስለዚህ አገራዊ ለውጣችን በመነጋገር ተጀምሮ በሀሳብ የበላይነት እንዲጠናቀቅ የሁላችንም ድርሻ ነው። መንግስት ብቻውን የሚያመጣው ለውጥ የለም። ጥቂት ሰዎች ብቻ ነደው የሚፈጥሩት እሳት የለም። በእሳቱ ለመሞቅ ሁላችንም ነዳጅ መሆን አለብን። እሳቱ ለውጥ ነው..ለውጥ ደግሞ በጋራ የሚመጣ የአብሮነት ሀይል ነው። የለውጥ መጀመሪያ መነጋገር ነው። የመነጋገር መጀመሪያ ደግሞ በሀሳብ የበላይነት ለመስማማት መዘጋጀት ነው። ይሄ ሁሉ ባልሆነበት ሜዳ ላይ የሚመጣ አገራዊም ሆነ ግለሰባዊ መሻሻል የለም። አሁናዊ ችግሮቻችንን በመነጋገር ካልፈታናቸው ሌላ በምንም አንፈታቸውም። ሲወቅስና ሲተች፣ ሲረግምና፣ ሲያንቋሽሽ የኖረ አእምሯችንን ለአዲስ ለውጥ ማሰልጠን ይኖርብናል። በጥላቻና በመገፋፋት የቆመ አካላችንን አብሮነትን ማልመድ ግድ ይለናል። ሌሎችን ባለማዳመጥ ዘመናትን የተሻገረውን ሰውነታችንን ማደስ ይኖርብናል። በራሱ ፍቅር የወደቀ እኛነታችንን ሌሎችን ማፍቀር እንዲለምድ በማድረግ ለውጣችንን እንጀምር።

ሆድ ከአገር ይሰፋል፤ አዎ ለተጠቀመበት ሆድ ከአገር ሰፊ ነው። ብዙ ነገር ይተዋል፤ ብዙ ነገር ይችላል። ችግራችን የመቻል፣ የመሸነፍ ጥበብ የለንም። ችግራችን ሳንገዳደል፣ ሳንወቃቀስ መዋደድ እንዳለብን አለማወቃችን ነው። አሸንፈን የበላይ ለመሆን ስለምንሞክር በመግባባት ውስጥ ያለውን የሰላም ስፍራ አልደረስንበትም። አያቴ በሕይወቷ ውስጥ ምንም ነገር ይከሰት በመተው የምትጽናና ሴት ነበረች። በመተው ማሸነፍ ደስታው ምን ያክል ይሆን? በመርሳት ከፍ ማለት ሰላሙ እስከ የት ይሆን? የዚህ ጥያቄ መልስ እያንዳንዳችን ውስጥ አለ፤ ነገር ግን አናውቀውም። ድረሱበት ስልም አደራ እላችኋለሁ። ለምንድነው በመነጋገር መግባባት ያቃተን? ለምንድነው መታረቅ ያቃተን? ለምንድነው መተቃቀፍ ያቃተን? ከፍ ብዬ እንዳልኳችሁ እኚህ ጥያቄዎች በድህ አገር ላይ ብዙ መልሶች አሏቸው።

እኛ አገር አብዛኞቹ ችግሮች ትላንት ወለድ ናቸው። በታሪክ የምንጣላ ብዙዎች ነን። ባልኖርንበትና በማናውቀው ትላንትና ውስጥ ገብተን በሰማንውና ባደመጥነው በጥቂት ግለሰቦች የውሸት ትርክት አይጥና ድመት የሆንን ብዙ ነን። ሰው እንዴት በማያውቀው ትላንት ይጣላል? የሆነው ሆኖ ላጣሉንም..እያጣሉን ላሉ ነገሮችም በመነጋገር ሰላም እናውርድ። ከሌላው ጋር ለመግባባት መጀመሪያ ከራሳችን ጋር መግባባት ይኖርብናል። ከራሱ ጋር የተግባባ ከሌላው ጋር ለመግባባት አይቸግረውም። የብዙዎቻችን ችግር ከራሳችን ጋር ሳንግባባ ከሌሎች ጋር ለመግባባት በጠረጴዛ ዙሪያ መቀመጣችን ነው። ከፈረሱ ጋሪው እየቀደመ ለዘመናት በከሰረ ፖለቲካ ውስጥ ነበርን። የከሰረ ፖለቲካ የከሰረ አገርና ትውልድ ከመፍጠር ባለፈ ጥቅም እንደሌለው ብዙ ቦታ አይተናል። መጀመሪያ ከራሳችን ጋር እንስማማ። መጀመሪያ የሀሳባችንን ፍሬ እንመዝን፣ መጀመሪያ አገርና ሕዝብ ይቅደሙ፤ ያኔ ሁሉም መልካም ይሆናል።

# የሀዲያ ብሔረሰብ ማህበረ-ባህላዊ ዕሴቶች

**ኢያሱ መሰለ**



ኢትዮጵያዊያን እንደ አገር የጋራ ሕግና መተዳደሪያ ደንብ አርቅቀን ጥቅም ላይ ከማዋላችን በፊት እንደየማህበረሰባችን ባህላዊ ዳራ ዲሞክራሲን፣ ፍትህን፣ እኩልነትን፣ አብሮነትን፣ እርቅን፣ ፍቅርና መቻቻልን ወዘተ ከእሴቶቻችን ተምረናል፤ ወርሰናልም። ባህላዊ እሴቶቻችን በየአካባቢው የሚኖረው ማህበረሰብ እርስ በእርሱም ይሁን ከሌሎች ማህበረሰቦች ጋር ጥሩ መስተጋብር ፈጥሮ እንዲኖር አስችለዋል። እንደ ጉዲፈቻ፣ ሞጋሳ፣ የጡት አባት፣ የአይን አባት የመሳሰሉት እሴቶች ማህበራዊ ትስስሩንና ስንስሉን የሚያጠብቅባቸው ገመዶቹ ናቸው። ኢትዮጵያ አንድነቷ ተጠብቆ እዚህ እንድትደርስ ያስቻላትም በየጊዜው በባህላዊ ወግና ሥርዓት የተገራ፣ የአባቶቹን ምክርና ተግሳጽ የሚሰማ፤ የማህበረሰቡን ወግና ባህል የሚያከብር ትውልድ ስለሚፈጠር የወረሰውን ትውፊትም አጠናክሮ ስለሚያስቀጥል ነው።

ኢትዮጵያዊያን በባህላችን መሰረት ሽማግሌዎቻችንን እናከብራለን፤ ፈጣሪያችንን እንፈራለን፤ እንግዳ እንቀበላለን፤ እንረዳዳለን፤ እርቅና ሰላምን እንወዳለን፤ ነውር የሆነ ድርጊትን፣ ግፍና በደልን እንጸየፋለን። ይህ ትናንት የነበረ፤ ዛሬም ያለ፤ ወደፊትም የሚኖር ማህበረ-ባህላዊ እሴታችን ያጎናጸፈን ታላቅ ጸጋ ነው።

በዛሬው የሀገርኛ አምዳችን ቅኝት ያደረግነው በሀዲያ ብሔረሰብ ባህላዊ እሴቶች ላይ ነው። በዋናነትም ማህበረሰቡ እርቅና ሰላምን ለማውረድ የሚጠቀምባቸው ባህላዊ ሥርዓቶች ጥልቅና ዝርዝር አፈጻጸሞች ያሉት ነው። እኛ ግን በወፍ በረር ምልከታ የፍትህና የእርቅ ስርዓቱን ለመዳሰስ ሞክረናል። በዚሁ መሰረት ከሰውና ከሰነድ የተገኘ መረጃ እንደሚከተለው ተጠናቅሯል።

‹‹ገራድ አድል ገብረ ኪዳን ቀልበጎ›› በሀዲያ ባህላዊ ሥርዓት ከአያት ቅድመ አያታቸው ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ስልጣን እንዲይዙ ማህበረሰቡ ሃላፊነት የሰጣቸው አባት ናቸው። ‹‹ገራድ አድል›› የሚለው የማዕረግ ስም ሲሆን የሀዲያ ብሄረሰብን በኃላፊነት ለሚመራ ሰው የሚሰጥ የክብር ስም ነው። ‹‹ገራድ›› ‹‹ገሩ አዶ›› ከሚሉት ቃላት ጥምረት የተገኘ ሲሆን፤ ትርጉሙም “የረጋ ወተት” ወይም “የበሰለ ሰው” ማለት ነው። ‹‹አድል›› የሚለውም “የፍትህ መሪ” ወይም “የፍትህ ንጉስ” እንደ ማለት ነው።

ገራድ አድል ገብረኪዳን ቀልበጎ የተወለዱት በሀዲያ ዞን አመካ ወረዳ፤ አንጃማ ተብሎ በሚጠራ ቀበሌ ነው። አንጃማ ማለት የአንድ ባህላዊ መሪ መቀመጫ ቦታ እንደ ማለት ነው። በወቅቱ ቦታው የአያታቸው መቀመጫ ስለነበር ይህን ስያሜ እንዳገኘና ቀበሌውም አንጃማ ተብሎ ለመጠራት እንደበቃ ገራድ አድል ገብረኪዳ ይገልፃሉ።

ገራድ አድል ገብረ ኪዳን ቀልበጎ በዚሁ አካባቢ እስከ ስምንተኛ ክፍል ተምረዋል። በወቅቱ ወደ ስልጣን የመጣው የደርግ መንግሥት ቤተሰቦቻቸው ላይ ግፍና በደል ይፈጽምባቸዋል። የተወሰኑ ቤተሰቦቻቸው ይረሸናሉ፤ አባታቸውም ይታሠራሉ፤ እርሳቸውም በልጅነታቸው ወደ አዲስ አበባ ለመሰደድ ይበቃሉ። ስማቸውን ቀይረው አዲስ አበባ ጀነራል ዊንጌት አካባቢ ተቀምጠው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ ለአራት ዓመት የቲዮሎጂ /የሥነመለኮት/ ትምህርት ተምረው ኬኒያና ኡጋንዳ እየተንቀሳቀሱ መንፈሳዊ ተግባራትን ይፈጽሙ ነበር። እግረ መንገዳቸውንም ሁለተኛ ዲግሪያቸውን ተምረው ያጠናቅቃሉ።

ገራድ አድል ገብረ ኪዳን እንደሚናገሩት፤ ከኢጣሊያን ወረራ በኋላ አያት ቅድመ አያታቸው ሲመሩት የነበረው ባህላዊ ሥርዓት በአጼ ኃይለሥላሴ ከዚያም ወዲህ በደርግ መንግስት ጫና ተፈጥሮበት ከአባት ወደ ልጅ ይደረግ የነበረው የስልጣን ሽግግር ወደ አባታቸው ሳይተላለፍ ይቀራል።

የአካባቢው ማህበረሰብ ግን ባህላዊ ሥርዓቱ እንዲቀጥል የገራድ አድል ገብረኪዳን አባት ማህበረሰቡን እንዲመሩት ይፈልጋል። እርሳቸው ግን በተለያዩ ምክንያቶች ማህበራዊ ሃላፊነትን ለመሸከም ፈቃደኛ ሳይሆኑ ይቀራሉ።

የኢህአዴግ መንግሥት ሥልጣን ከያዘ በኋላ ለባህላዊ እሴቶች ዋጋ መስጠቱን ተከትሎ የማህበረሰቡ ባህላዊ ሥርዓቶች እንደገና ማንሰራራት ይጀምራሉ።

የሀዲያን ማህበረሰብ ሲመሩ ከነበሩ ሰዎች መካከል ማህበረሰቡን የሚመራ ሰው እንዲመረጥ ይደረጋል። በዚሁ መሰረት ገራድ አድል ገብረ ኪዳን ቀልባጎ እስከ አያታቸው ዘመን ድረስ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ሥርዓት እንዲያስቀጥሉ ለ‹‹አሽን ገራድ›› ይታጫሉ። ሥርዓተ ሹመቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ‹‹ሄቦ... ሄቦ... አሽን ገራድ›› ተብሎ ስልጣናቸው ይታወጃል።

ከአምስት ዓመት በኋላ ደግሞ በመላው ኢትዮጵያ ያሉ አጠቃላይ የሃዲያ ገራድና የሌሎችም ብሔረሰቦች፣ የአገር ሽማግሌዎችና ባለስልጣናት በተገኙበት በአዲስ አበባ ከተማ ‹‹ገራድ አድል›› የሚለው ከፍተኛ ማእረግ ይሰጣቸዋል።

በዚህ ርእሰ ጉዳይ ትኩረት ያደረግነው የገራዳዊ ሴራ ታሪካዊ አመጣጥና አወቃቀር ላይ ሳይሆን የሀዲያ ብሔረሰብ እርቅና ሰላምን ለማውረድ የሚጠቀምባቸው ማህበረ-ባህላዊ እሴቶች ላይ ነው።

ዘመናትን የተሻገረው የገራድ ማህበረ-ባህላዊ ሥርዓት የብሄረሰቡን ተወላጆች ብቻ ሳይሆን እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎችንም ያቅፋል። የዲሞክራሲ፣ የፍትህ፣ የእርቅ፣ የሰላም የሀዘን፣ የደስታ ወዘተ ማህበራዊ መስተጋብሮች በባህሉ መሰረት እንዲከወኑ ያደርጋል።

ገራድ በሥሩ አምስት መዋቅሮች አሉት። መዋቅሩን ከታች ወደ ላይ ስንመለከተው ሚንዳና፣ ሞልዳና፣ ሱልዳና እና ጊቾዳና ናቸው።

በማህበረሰቡ ውስጥ የሚፈጠሩ ግጭቶች ወይም ችግሮች እንደ ክብደትና ቅለታቸው መጠን በየደረጃው በተዋቀሩ ተወካዮች እንዲታዩ ይደረጋል። በቤተሰብ መካከል ከሚፈጠሩ አለመግባባቶች ጀምሮ አጠቃላይ የሀዲያ ብሔረሰብ ከሌሎች ብሔረሰቦች ጋር ግጭት ውስጥ ቢገባ ገራዶች እየመከሩ መፍትሄ ይሰጣሉ።

እንደ ገራድ አድል ገብረኪዳን አባባል የሀዲያ ሕዝብ የዲሞክራሲ፣ የፍትህ፣ የሰላም እና የሌሎችንም ማህበራዊ ጉዳዮች ከአምስት መቶ አመት በፊት ጀምሮ በባህላዊ ሥርዓት ሲፈጽም የኖረ ነው። ሀዲያ ከእርሱ ጋር የሚኖሩ ሌሎች ብሄረሰቦችንም በባህላዊ ሥርዓቱ ያቅፋል። በባህሉ መሰረት ጡት መጣባት አለ። ጡት የተጣባ ሌላ ብሔረሰብ እንደ ወንድም ወይም እንደ ሀዲያ ብሔረሰብ አባል ይታያል። ለምሳሌ በሀዲያ ብሔረሰብ ስድስት ጎሳዎች /የዘር ግንዶች/ አሉ። የአማራ ተወላጆች ወደ ሥፍራው መጥተው መኖር ሲጀምሩ ሀዲያ እነዚህን አካላት እንደ ሰባተኛ ጎሳ አድርጎ ተቀበላቸው እንጂ አልገፋቸውም ይላሉ ገራድ አድል ገብረ ኪዳን። ጡት ተጣብተው በሀዲያ ብሄረሰብ ወግና ባህል መሰረት እየኖሩ ነው። ምርቃት ላይ ሰባተኛ ወንድም ተነስተህ መርቅ ይባላሉ።

የሀዲያን ቋንቋ ወግና ሥርዓት እያከበሩ ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ተስማምተው እየኖሩ ነው። ስለዚህ ሀዲያ ለራሱ ብሄረሰብ ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም ተገቢውን እውቅና ይሰጣል። አሁን በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ዘርን መሰረት ያደረጉ ግጭቶች ሲፈጠሩ ሀዲያ ውስጥ ኮሽታ የሌለው ሌላውንም እንደራሱ አድርጎ ስለተቀበለ ነው። ይህ ታዲያ ሀዲያ ለዲሞክራሲ ሥርዓት አዲስ አለመሆኑን ያሳያል። የሀዲያ ሕዝብ ለዘመናት ሲያራምድ በነበረው ባህላዊ ሥርዓት የዲሞክራሲ፣ የፍትህና የእኩልነት አስተሳሰቦችን አዳብሯል።

በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ስለ ፍትህ ስለ ዲሞክራሲ የሚታገሉ ጎምቱ ፖለቲከኞችና የታሪክ ተመራማሪዎች ከዚህ ማህበረሰብ ወጥተዋል። እንደ ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስና እንደ ፕሮፌሰር ላፒሶ ጌ.ዴሌቦ የመሳሰሉትንና ሌሎች በርካቶችን መጥቀስ ይቻላል።

እንደ ገራድ አድል ገብረኪዳን እንደሚሉት እነዚህ ምሁራን የታሪክ፣ የዲሞክራሲ፣ የፍትህ፣ የሰላም ወዘተ እውቀትን ከማህበረሱ ባህላዊ ሥርዓት እየተማሩ ያደጉና ከባህሉ የተቀዳ ማንነትን ያጎለበቱ ናቸው።

የኢህአዴግ እጩዎች ለበርካታ ጊዜ ከማይመረጡበት አካባቢ አንዱ ሀዲያ ነበር ያሉት ገራድ አድል ገብረ ኪዳን ይህ የሚያሳየን የሀዲያ ሕዝብ ለእውነተኛ ዲሞክራሲና ለሰው ልጆች መብት መከበር የቆመ መሆኑን ነው። የሀዲያ ሕዝብ በጎሰኝነት፣ በጎጠኝነት፣ በዘረኝነት ... ፖለቲካ እንዳይጠላለፍና ፍትሃዊ እንዲሆን ያደረገው ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው ማህበረ-ባህላዊ እሴቱ ነው። በመሆኑም የሀዲያ ሕዝብ እሴት ለሌሎች አካባቢዎችም ምሳሌ መሆን የሚችል ሀብት ነው።

አሁን አሁን ይህንን ድንቅ ባህል ሊያደበዝዙ የሚሞክሩ አሠራሮች እየታዩ ስለሆነ ሊታረሙ እንደሚገባ መጠቆም ያስፈልጋል ይላሉ ገራድ አድል ገብረኪዳን።

እንደ ገራድ አድል ገብረኪዳን አባባል ባህላዊ ተቋማት ህጋዊ መሰረት ቢኖራቸው አሁን እየታየ ላለው አገራዊ ችግር መፍትሄ ማመንጨት በቻሉ ነበር። ከሰማኒያ አምስት በላይ የሚሆኑ ብሄረሰቦችን ባህልና እሴት ወደ ጎን ትቶ የውጭ አገር ልምድን መሰረት ባደረገ ሕገ መንግስት አገርን መምራት አስቸጋሪ ነው። አገራዊ እሴቶች እየተጠኑ ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚያደርግ ኢንስቲትዩት ሊኖር ይገባል። ‹‹ወፍ እንደአገሯ....›› እንዲሉ ለአገራዊ ችግሮቻችን አገራዊ መፍትሄዎችን ማስቀደም ያስፈልጋል።

ለምሳሌ የኦሮሞ ገዳ ሥርዓት፣ የሀዲያ ገራዳ ስርዓት፣ የጋሞ፣ የሲዳማ፣ የአማራ፣ የወላይታ ወዘተ እሴቶች በአግባቡ ጥቅም ላይ ቢውሉ ችግሮቻችንን መቅረፍ ያስችሉናል። ሽማግሌዎች የመንግሥት ፖለቲካዊ ጉዳይ አስፈጻሚ መሆናቸውን ትተው እንደ ባህሉ፣ ወግና ሥርዓቱ ሕዝባቸውን እየመሩ ተሰሚ መሆን ይገባቸዋል። የአገር ሽማግሌዎች የሚደመጡና የሚከበሩ እንዲሆኑ ከተፈለገ ከመንግሥት ተጽዕኖ መላቀቅ አለባቸው። በመንግሥትና በሕዝብ መካከል አለመግባባት ቢፈጠር እንኳ ሽማግሌዎች ሕዝባቸውን ማረጋጋትና እሳት ማጥፋት የሚችሉት የሕዝብ ድጋፍ ሲኖራቸውና ከመንግሥት ተፅዕኖ ነጻ መሆናቸው ሲታመን ነው ብለዋል።

ገራድ አድል ገብረኪዳን ከፍትህ አንጻር የሀዲያ ብሔረሰብ ከመንግሥት የፍትህ ተቋም ይልቅ በባህላዊ የፍትህ ስርዓቱ ላይ እምነት አለው ይላሉ። ለምሳሌ በመንግሥት የፍትህ መዋቅር ዳኞች ተጨባጭ መረጃ ከሌላቸው ፍርድ አይሰጡም። በሀዲያ ማህበረሰብ እውነትን ገላልጦ በማውጣት በዳይን ለመውቀስ ተበዳይን ለመካስ የሚያስችል ባህላዊ የፍትህ ሥርዓት አለ። በተለይም ነፍስ ከጠፋና ወንጀሉን የፈጸመው ሰው ካልታወቀ ጥፋት አድርሰዋል ተብለው የተጠረጠሩት ሰዎች ጉዳዩን ስለመፈጸማቸውና አለመፈጸማቸው ቃለ መሃላ ያደርጋሉ። መሃላው ጥቁር መውጋት /ሄመቻ ቀስማ/ ይባላል።

ተጠርጣሪው ጥቁር ከብት እየወጋና ደሙን እያፈሰሰ አልገደልኩም፤ ከገደልኩ ደሜን እንደዚህ ያፍስሰው፤ በወንጀሉ እጄ ካለበት የተረገምኩ ልሁን፤ እያለ ቃለ መሃላ የሚፈጽበት ባህላዊ ሥርዓት ነው። በዚህ አያበቃም፤ ሳር የማያበቅል ገላጣ ቦታና የእንቧይ ዛፍ ወዳለበት ቦታ ይሄዳል። በብሔረሰቡ እምነት የእንቧይ ዛፍ ከዛፎች ሁሉ አጭሩና የተናቀ ነው፤ ለጣውላ፣ ለማገዶ፣ ለጥላ የማያገለግል እሾሃማ ነው። ስለዚህ ተጠርጣሪዎቹ በእንቧይ ላይ እንዲሸኑ ይደረጋል። ገራድ አድል ገብረኪዳን እንደሚያስረዱት “ወንጀሉን ከፈጸምነው ዘራችን እንደዚህ እንቧይ ለምንም የማይጠቅም ይሁን” የሚል አንድምታ አለው።

መሃላው ይደርሳል ተብሎ በጽኑ ስለሚታመን ሰዎች ሳይዋሹ እውነታውን ይናገራሉ። ተጠርጣሪው እውነታውን ለመሸሸግ አይደፍርም፤ እውነታው ከታወቀ በኋላ ተበዳይ ትክክለኛውን ፍትህ እንዲያገኝ ይደረጋል ማለት ነው። ከዚህ በኋላ የተለያዩ ባህላዊ ሂደቶች ተከናውነው እርቅ ይደረጋል። የእርቅ ስርዓቱ “የጢግ ጉላ ሥነ ሥርዓት” ይባላል።

አለባቸው ኬዕሚሶ እና ሳሙኤል ሀንዳሞ እንዳጻፉት ‹‹በሀዲያ ማህበረሰብ ‹የጢግ ጉላ› ሥነ ሥርዓት የጥል፣ የበቀልና የጸጸት ስሜትን በማንጻት ወደ ሰላማዊና ጤናማ ግንኙነት የመመለስ ሥነ ሥርዓት ነው። የጢግ ጉላ ሥርዓት ለሟች ቤተሰብና ለገዳይ ቤተሰቦች የሥነ ልቦና ፈውስ ይሰጣል›› ይላሉ ።

የበዳይና የተበዳይ ቤተሰቦች ወንዝ ወርደው ወተትና ማር በአንድ እቃ እንዲጠጡ ይደረጋል። ተበዳይ ካሳ እንዲያገኝ ይደረጋል። ገዳይ የሟች ቤተሰብ ይሆንና መሬት ተሰጥቶት እያረሰ እንደ ልጅ የሟችን ቤተሰብ ያግዛል። ተበዳይም ቂሙን እርግፍ አድርጎ ይተዋል፤ ከዚያ በኋላ ሰላም ይሰፍናል ማለት ነው።

በሀዲያ ብሔረሰብ እንደመተውና እንደመስጠት በምድር ጸጋ የለም ተብሎ ስለሚታመን ሰዎች ቂማቸውን ይተዋሉ። ማህበረ-ባህላዊ እሴቱ ለዘመናት በሀዲያ ምድር ሰላም እንዲሰፍን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከተ በመሆኑ ልምዱና ተሞክሮው በአገራዊ ምክክሩና መግባባቱ ተጠቃሽ ቢሆን ሌሎች ሊማሩበት ይችላሉ ብለዋል ገራድ አድል ገብረኪዳን ቀልበጎ።

ቅራኔዎችን በባህላዊ መንገድ የመፈታት ልምዳችን ቢዳብር የኢትዮጵያ ዛሬ ያንዣበበት አደጋ ባልኖረ ነበር። እኛም የሀዲያ ማህበረ-ባህላዊ የእርቅና ሰላም ሥነስርዓት ለአገራዊ ምክክርና መግባባት የራሱን ድርሻ ስለሚያበረክት ሊበረታታ ይገባል እያልን ተሰናበትን። ቸር እንሰንብት።

ማህበራዊ

# ወጣቶች

## የፖሊሲ ማዕቀፍ ለወጣቶች

አስናቀ ፀጋዬ

ኢትዮጵያ በርካታ ቁጥር ያለው ወጣት የሚገኝባት አገር ናት። ይህ ቁጥር ታዲያ አንድም እንደ መልካም እድል ሁለትም እንደ ስጋት ይቆጠራል። በርካታ ቁጥር ያለው ትኩስ ሃይል ወደ ሥራ ቢሰማራ የአገሪቱን ኢኮኖሚ በእጅጉ የሚያሳድግ በመሆኑ እንደመልካም አጋጣሚ ሊቆጠር ይችላል። ከዚህ በተቃራኒ ደግሞ ለዚህ ትኩስ ሃይል በበቂ ሁኔታ የሥራ እድል መፍጠር ካልቻለ መልሶ ስጋት የሚሆንበት እድል ሰፊ ነው።

መንግሥት በተለያዩ ጊዜያት ለወጣቶች የሥራ እድል ለመፍጠር በርካታ ጥረቶችን ቢያደርግም የሚጠበቀውን ያህል አመርቂ ውጤት አላመጣም። የወጣቱ ተደጋጋሚ የሥራ እድል ጥያቄም በቂ ምላሽ ባለማግኘቱ ወደ ተቃውሞ ተሸጋግሮ ከዛሬ አራት ዓመት በፊት የመንግሥት ለውጥ አስከትሏል።

ባለፉት አራት ዓመታት የለውጡ መንግሥት በብዙ መናወጥ ውስጥ ሆኖ ለወጣቱ የሥራ እድል ለመፍጠር መጠነኛ ጥረቶችን ቢያደርግም ጀመረው እንጂ ገና ብዙ ይቀረዋል። በተለይ ደግሞ ወጣቱ የራሱን ሥራ እንዲፈጥር ማበረታቻዎችንና ድጋፎችን ከማድረግ አኳያ የጀመራቸውን እንቅስቃሴዎች አጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት የብዙዎች አስተያየት ነው። በዋናነት ደግሞ መንግሥት ለሥራ ፈጠራ አስፈላጊ የሆኑ የፖሊሲ ማዕቀፎችን ማዘጋጀት እንደሚገባው በዚህ ዘርፍ ያሉ ባለሙያዎች ይጎተጉታሉ።

አቶ መቅደላ መኩሪያ በቅድስተ ማሪያም ዩኒቨርሲቲ የማርኬቲንግ መምህርና በኢምፓክት የኢንተርፕረነርሺፕ ፕሮግራም የቢዝነስና የፋይናንስ አማካሪ ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት ሥራ ፈጠራን ማበረታታትና ማስፋት የሚቻለው በትምህርት ፕሮግራሞች፣ በተለያዩ የሚዲያ ዝግጅቶችና መድረኮች ላይ በማካተትና ዓላማ አድርጎ በመስራት ነው።

የሥራ ፈጠራን በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ብቻ አካቶ ማስተማር ሳይሆን ከመጀመሪያ ደረጃ ጀምሮ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ድረስ ልጆች እንዴት ሥራን መፍጠር እንደሚችሉ ትምህርት መስጠት ያስፈልጋል።

የትምህርት ሥርዓቱ፣ የሚዘጋጁ የሬዲዮ፣ ቴሌቪዥንና የጋዜጣ ፕሮግራሞች ችግር ላይ ብቻ አተኩረው መፍትሄ የማያሳዩ ከሆነ አሁን የሚታዩ የስራ አጥ ችግሮች እየተባባሱ ይሄዳሉ። የትምህርት ተቋማትም የተማሪዎችን ክሂሎት ማዳበር ላይ ብቻ እንጂ ክሂሎታቸውን መመንዘር የሚያስቻለቸው ብቃት እንዲኖራቸው እየሰሩ አይደሉም።

ከዚህ አንፃር በተለይ ሥራ አጥነትን ለመቀነስና ከተቀጣሪነት አባዜ ለመላቀቅ ችግሮችን ከመስበክ ይልቅ ችግሮችን በማሳየት መፍትሄ ማምጣት የሚችል አእምሮ ላይ መሥራትና መኮትኮት ያስፈልጋል። ሚዲያዎችም በሥራ ፈጠራ ላይ ትኩረት አድርገው ሊሰሩ ይገባል። ተቋማትም ማሕበረሰቡ ላይ መስራት ይጠበቅባቸዋል።

ወጣቶችም ከተቀጣሪነት አስተሳሰብ ወጥተው ሥራ ፈጣሪ እንዲሆኑ ሥራን የመስራት ባህልና ሥራን ማክበር ተቀዳሚ ተግባራቸው ሊሆን ይገባል። ይህም ለመስራት ካሰቡት ጋር የተገናኘ ተቋም ላይ ሄደው በነፃ ማገልገልን ይጨምራል። ከዚህ በተቃራኒ እጎዳለሁ ብለው የሚያስቡ ከሆነ ሥራ መፍጠር አይችሉም።

ሥራ ለመፍጠርና አዲስ መንገድ ለማምጣት ጊዜያቸውን በሥራ ላይ ማዋል ይኖርባቸዋል። ለሚያመጡት ሃሳብ ሌሎች የተሻለ መንገድ አላቸውና ከእነሱ ምን እማራለሁ ብሎ ማሰብም ያስፈልጋል። አለማወቃቸውን ሲያውቁም ነው ወጣቶች የተሻለ ቦታ መምጣት የሚችሉት።

እንደአማካሪው ገለፃ ሥራ ለመፍጠር በአብዛኛው የተመቹ ፖሊሲዎች አሉ። ሥራውን ማስቀጠል ላይ ፖሊሲዎቹ ምን ያህል ያግዛሉ የሚለውን ግን መፈተሽ ያስፈልጋል። ንግድ ፍቃድ ማውጣት ቀላል ቢሆንም ንግዱን ማሻገርና ማስኬድ ሲፈለግ ግን በርካታ እንቅፋቶች አሉ። በዚህ ረገድም ብዙ መሥራት ያስፈልጋል።

በእያንዳንዱ የሥራ ፈጠራ ዘርፎች ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት የምክክር መድረኮችን በየጊዜው ማዘጋጀት ያስፈልጋል። አልፎ አልፎ በተቋማት ደረጃ ነጋዴንና የንግድ መፍትሄ ሃሳብ ይዘው የመጡ ተቋማትን በጅምላ የማየት ችግሮች ይታያሉ። እንዲህ አይነቱ አመለካከት ካለ ደግሞ ጎታች በመሆኑ ማስቀረት ይገባል።



አቶ ጳውሎስ መርጋ፣



ለማወርቅ ዴክሲሶ፣



አቶ መቅደላ መኩሪያ፣

> ሥራ ለመፍጠርና አዲስ መንገድ ለማምጣት ጊዜያቸውን በሥራ ላይ ማዋል ይኖርባቸዋል። ለሚያመጡት ሃሳብ ሌሎች የተሻለ መንገድ አላቸውና ከእነሱ ምን እማራለሁ ብሎ ማሰብም ያስፈልጋል። አለማወቃቸውን ሲያውቁም ነው ወጣቶች የተሻለ በታ መምጣት የሚችሉት።

ሌሎች አገራት የሥራ ፈጠራን ማሳደግ የቻሉት የንግድና አዳዲስ ሃሳቦችን ወደ ገበያ መምጫ መንገዶችን ስላቀለሉና የማዝለቂያ መንገዶችንም በማመቻቸታቸው ነው። ከዚህ አኳያ በነዚህ ነገሮች ላይ መስራት ያስፈልጋል። ይህ ሲባል ግን የመንግሥት ተቋማት ግዴታ ብቻ ነው ማለት አይደለም። ሁሉም በዚህ ዘርፍ ላይ ያሉ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት በተለይም የፋይናንስ፣ ሎጀስቲክስና የተለያዩ የንግድ ተቋማት የየራሳቸውን ሚና መጫወት አለባቸው።

በብሩማይንድስ አማካሪ ድርጅት ከፍተኛ የፕሮግራም አስተባባሪ አቶ ለማወርቅ ዴክሲሶ እንደሚሉት ድርጅቱ የፕሮጀክቶችን መነሻ ዳሰሳዎችን፣ የአጋማሽና መጨረሻ ምዘናዎችን እንዲሁም የማማከር ሥራዎችንና ሥልጠናዎችን ይሰጣል። የቢዝነስ ልማት አገልግሎትና ሥራ ፈጠራ ላይም ትኩረት አድርጎ ይንቀሳቀሳል።

ድርጅቱ ከተመሰረተ ወዲህ በየወሩ ‹‹ልዩ ምልከታ›› በሚል የሥራ እድል ፈጠራና የወጣቶች ሥራ ፈጣሪነትን ለማሻሻልና ለማስፋፋት ብሎም ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር ላይ ዓላማ ያደረገ የውይይት መድረክ ያካሂዳል። በዚህ ወርም የመንግሥት አካላት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የልማት አጋሮችና የግል ተቋማት ተቀናጅተው የሥራ እድል ፈጠራን ማስፋት እንዲቻል የምክክር መድረክ አካሂዷል።

እንደ አስተባባሪው ገለፃ በመጀመሪያው የውይይት መድረክ በወጣቶች የሥራ እድል ፈጠራ ዙሪያ የፖሊሲ ማእቀፍ ክፍተት እንዳለ ለማወቅ ተችሏል። በዚህ ዙሪያ በመንግሥት፣ የግል ተቋማትና ድርጅቶች መካከል ተቀናጅቶ ያለመስራት ችግሮችም እንደሚታዩ ተረጋግጧል። ሆኖም በዚህ መድረክ እነዚህ ተቋማት በሥራ እድል ፈጠራ ዙሪያ ተቀናጅተው የሚሰሩበትና ለፖሊሲ ግብአትነት የሚውሉ ነጥቦች ተገኝተውበታል።

የሥራ እድል ፈጠራ ጉዳይ ብሩማይንድስን ጨምሮ ሁሉንም ባለድርሻ አካላት የሚመለከት በመሆኑ በሁለተኛው የውይይት መድረክ የበለጠ ግብአት ተሰብስቧል። ይህም ግብዓት የንግድ ፈጠራ የፖሊሲ ማእቀፍ እንዲኖረው አስተዋፅኦ ይኖረዋል ተብሎ ይጠበቃል።

ከዚህ በላፈ በመድረኩ የተሳተፉ ሥራ ፈጣሪዎችና ሥራ ለመፍጠር በዝግጅት ላይ ያሉ የዩኒቨርሲቲ ምሩቃን የሥራ እድል ፈጠራን በምን መልኩ ማስኬድ እንደሚቻል ግብዓት አግኝተውበታል።

በዚህ የውይይት መድረክ የተሳተፉት በተለያዩ ፕሮጀክቶች ታቅፈው ሥልጠና የሚወስዱ ወጣቶች ሲሆኑ በቀጣይ በሚዘጋጁ ተመሳሳይ መድረኮች ለሌሎች ወጣቶች ተደራሽ ለማድረግ በድርጅቱ በኩል እቅድ ተይዟል።

በኢትዮጵያ ትልቅ የሥራ እድል ፈጠራ አቅም ቢኖርም በዚህ ልክ የሥራ እድል ፈጠራው አላደገም። ለዚህም የፖሊሲ ማዕቀፍ አለመኖር፣ መሬት የማሕበራዊና ፖለቲካዊ ተፅእኖ ያለው መሆንና ሌሎችም በምክንያትነት ይጠቀሳሉ።

ከዚህ አንፃር የአሁኑን ጨምሮ በቀጣይ በሚካሄዱ ተመሳሳይ መድረኮች ከአካዳሚክና የምርምር ተቋማት፣ ከፖሊሲ አውጪዎችና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ሃሳብ በመውሰድና ይህንኑ በማቀናጀት እሚያግባቡ ጉዳዮች ላይ መድረስ ያስችላል።

የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ጳውሎስ መርጋ በበኩላቸው እንደሚገልጹት ተቋሙ በአዲሱ የመንግሥት አደረጃጀት ከአነስተኛና መካከለኛ ልማት ኤጀንሲ ወደ ኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ተቀይሯል። የዚህ ተቋም ዋነኛ ዓላማም ኢንተርፕራይዞችን በመደገፍ ኢትዮጵያ በቀጣዩ አስር ዓመት የአምራች ኢንዱስትሪ ሽግግር ለማምጣት የምታደርገውን ጥረት ማገዝ ነው።

ከዚህ አኳያም ተቋሙ በተለይ ወጣቶች ሥራ ፈጣሪ እንዲሆኑ በአስተሳሰብና አመለካከት መለወጥ ላይ ይሰራል። ለሥራ አድል ፈጠራ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፤ አዳዲስ ፖሊሲዎችን ይቀርፃል። ለአምራች ኢንዱስትሪውም የፋይናንስ፣ የመሬት፣ የማምረቻ ሼዶች አቅርቦትና ቴክኒካል ድጋፎችን ያደርጋል። ከኤክስፖርት ገበያው ጋር በተያያዘም የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ ወጣቶች በኢኮኖሚው ውስጥ ያላቸውን አስተዋፅኦ ለማሳደግ ይሰራል።

ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ እንደሚሉት የአገሪቱ አብዛኛው ኢኮኖሚ በግብርና ላይ የተንጠለጠለ እንደመሆኑ እስካሁን ባለው ሂደት በአገር አቀፍ ደረጃ 22ሺህ 800 አነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች በተለያዩ ክልሎች ተፈጥረዋል። በእነዚህም ከ600 ሺህ በላይ የሥራ አድሎች ተፈጥረዋል። ተጨማሪ አዳዲስ ኢንትርፕራይዞችም እየተፈጠሩ ይገኛሉ። ወደ ኤሜሪካና አውሮፓ ምርቶቻቸውን የሚልኩ ኢንተርፕራይዞችን መፍጠር ተችሏል። በተለይ በኮቪድ ጊዜ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛዎችን፣ የእጅ መታጠቢያዎችንና ሳኒታይዘሮችን በማምረት ትልቅ አስተዋፅኦ አድርገዋል።

በተመሳሳይ በጨርቃጨርቅ፣ ቆዳ ምርትና በተቀነባበሩ የግብርና ምርቶችም ከፍተኛ እድገቶች ታይተዋል። ይሁንና አገሪቱ ካላት አጠቃላይ አቅምና የሕዝብ ብዛት አንፃር እስካሁን ያለው አድገት በጣም አነስተኛ ነው። ይህንኑ ሁኔታ ለመቀየርም በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ደረጃ የአምራች ኢንዱስትሪ ፖሊሲ ተዘጋጅቶ በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል። ይህም ኢንተርፕራይዞችን ያበረታታል፤ ምቹ ሁኔታም ይፈጥራል። አላሰራ ያሉ ውጣ ውረዶችን፣ የፋይናንስ አቅርቦት፣ የመሰረተ ልማት አቅርቦት ችግሮችን በፍታት ረገድ ለውጥ ያመጣል ተብሎ ይጠበቃል።

ኢትዮጵያ ሰፊ ወጣት (ከአጠቃላይ ሕዝቡ 70 በመቶ) የሰው ሀብት ያላት አገር እንደመሆኗ ይህ ትልቅ ገበያ በመሆኑ ሀብቱን በስፋት ጥቅም ላይ ማዋል ይገባል። በሌላ በኩል ደግሞ አገሪቱ እምቅ የተፈጥሮ ሀብት ያላት በመሆኑ ይህን ሀብት በስፋት ለመጠቀም ወጣቶችን ከዚህ ሀብት ጋር በሕግ ማእቀፍ ማስተሳሰር ያስፈልጋል። ይህም ከውጭ አገር የሚገቡ በርካታ ምርቶችን ማስቀረት ያስችላል።

ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ እንደሚናገሩት ቀደም ሲል የኢንዱስትሪ ፖሊሲ በ1994 ዓ.ም ተዘጋጅቶ ነበር። ሆኖም የወቅቱ ሁኔታን ባገናዘበ መልኩ ፖሊሲው መሻሻል ስላለበት በአሁኑ ጊዜ ወቅቱን በሚመጥን መልኩ እየተሻሻለ ይገኛል። መንግሥትም በራሱ ተነሳሽነት ባደረገው ልዩ ውሳኔ የወታደር የደምብ ልብሶች፣ የተማሪ የደምብ ልብሶችና ጫማዎች፣ የፖሊስና የልዩ ሃይል ደምብ ልብሶች በአገር ውስጥ እንዲመረቱ ተደርጓል። መንግሥት የአገር ውስጥ ምርትን ወደ መጠቀም እያዘነበለ በመሆኑና ይህም በቀጣይ እየተጠናከረ ሲሄድ ትልቅ ለውጥ ያመጣል ተብሎ ይጠበቃል።

# የምድር በረከት

## ከማዕድኖች ሁሉ ማዕድን የሚገኝበት ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ

ስምስም መንግሥቱ

**ከዚህ ቀደም በደቡብ ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት ሥር ነበር። በቅርቡ የተካሄደውን ሕዝበ ውሳኔ ተከትሎ ግን እራሱን ችሎ 11ኛ የኢትዮጵያ ክልል ሆኗል። ቀድሞ በደቡብ ክልል ሥር በተለያየ መዋቅር ሥር የነበሩትን የኮንታ ልዩ ወረዳ ፣ የምዕራብ ኦሞ፣ የቤንች ሸኮ፣ የካፋ፣ የዳውሮና የሸካ ዞኖችን በአንድነት በመያዝ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ሆኖ ተመስርቷል። እራሱን በራሱ ማስተዳደር ከጀመረም የአጭር ጊዜ ቆይታ ነው ያለው። በዚህ ጊዜ ውስጥ በማሕበራዊ፣ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መስክ የተጠናከረ አደረጃጀት ለመመስረት ጊዜው ገና እንደሆነ ይታመናል። ይሁን እንጂ ፈጥኖ ወደ ሥራ በመግባት የሚከናወኑ ተግባራት እንዳሉም ይጠበቃል። በተለይም የኢኮኖሚ አቅምን ከመገንባት አንጻር ለሚያስተዳድረው ሕዝብ አቅም መፍጠር ከቀዳሚ ተግባራቱ መካከል እንደሚሆንም ይታሰባል።**

**የደቡብ ምእራብ ክልል የኢኮኖሚ አቅምን ሊገነቡ ከሚያስችሉት እምቅ ሀብቶቹ መካከል የተለያዩ ማዕድናት ይጠቀሳሉ። ለግንባታ፣ ለኢንደስትሪ፣ ለተለያዩ ጌጣጌቶች የሚውሉ ሀብቶች የያዘ አካባቢ ነው። በተለይም በከፍተኛ ደረጃ ለአገር ኢኮኖሚ ዕድገት የውጭ ምንዛሪ በማምጣት ጉልህ ሚና ያለው የወርቅ ማዕድናት ባለቤትም እንደሆነ ይነገራል። ለአካባቢ ዜጎች የሚፈጥረው የሥራ ዕድልም ከፍተኛ መሆኑ ይታመናል።**

**የዝግጅት ክፍላችንም በዛሬው የምድር በረከት አምድ ላይ ዋንኛ ማጠንጠኛውን በክልሉ የማዕድን ዘርፉ ያለውን አያሌ ጠቀሜታ ታሳቢ ባደረ እየተከናወነ ስላለው ተግባር ለመዳሰስ ወድዷል። ለዚህ እንዲረዳን በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ማዕድንና ኢነርጂ ልማት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ከሆኑት ኢንጂነር ፍቅሬ ኃይሌ ጋር ቆይታ አድርገናል። መልካም ቆይታ!**

**አዲስ ዘመን፡- ክልሉ ያሉትን ዋና ዋና የማዕድን ሀብቶችና ጥቅም ላይ ለማዋል የተዘረጋውን አሰራር ቢገልጹልን**

**ኢንጂነር ፍቅሬ፡-** የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ከተመሰረተ ገና አጭር ጊዜ ቢሆንም ወደ ሥራ ፈጥኖ በመግባት የተለያዩ ተግባራትን በማከናወን ላይ ይገኛል። ከማዕድን ዘርፍ ሥራዎች አንጻር እየተከናወኑ ያሉ ተግባራትን ስንቃኝ፤ እንደአገር በተያዘው የአስር ዓመት ዕቅድ ትኩረት ከተሰጣቸው ዘርፎች አንዱ የማዕድን ዘርፍ ነው። ይህ ዘርፍ በአገር ኢኮኖሚ ውስጥ ጉልህ ድርሻ እንዲኖረው በክልሉ ያለውን እምቅ ሀብት ጥቅም ላይ ለማዋል ጥረት ለማድረግ እንቅስቃሴዎች ተጀምረዋል። ለምሳሌ ያህል በ9 ወር ጊዜ ውስጥ 214 ኪሎ ግራም ወርቅ ብሄራዊ ባንክ አስገብቷል። እንዲህ ያለውን አስተዋፆ ማበርከት የተቻለው በባህላዊ ወርቅ አመራረት ዘዴ ነው። የልማቱ ሥራ ቢዘምንና ሀብቱ በጥናትን ምርምር ተለይቶና ተደራጅቶ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ ቢቻል ተጠቃሚነቱ ከፍተኛ እንደሚሆን መገመት አያዳግትም። ክልሉ ወርቅን ጨምሮ የተለያዩ ማዕድናት ባለፀጋ ቢሆንም ልማቱ እየተከናወነ ያለው በባህላዊ መንገድ ነው። በዚህ የተነሳም ክልሉ እራሱን ችሎ መንቀሳቀስ ከመጀመሩ በፊትም ለዘርፉ ትኩረት ተሰጥቶ እምቅ ሀብቱ ከባህላዊ አሰራር ወጥቶ በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል ባለመደረጉ የሚፈለገውን ያህል ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አላስገኘም።

የማዕድን ሀብቶችን ለይቶና አደራጅቱ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ የክልሉ ቀጣይ የቤት ሥራ እንደሆነ ግንዛቤ ተይዞ ከወዲሁ እየተሰራ ነው። በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ከውጭ ወደ አገር ውስጥ የሚገባውንም በአገር ውስጥ በመተካት ተጠቃሚነትን ማሳደግ ስለሚያስፈልግ ትኩረት ሰጥቶ ልማቱን ማጠናከር ግድ ይላል።

ከወርቅ ማዕድን በተጨማሪ ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚውል የድንጋይ ከሰል በክልሉ ዳውሮና ኮንታ ዞኖች በስፋት ይገኛል። ይህ ሀብት በተለይ ለሲሚንቶ አምራች ኢንዱስትሪዎች በከፍተኛ ሁኔታ ይጠቅማል። ሀብቱ ጥቅም ላይ ቢውል በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ በግዥ ወደ አገር የሚገባውን ምርት መተካት ይቻላል። ይህን ታሳቢ በማድረግ በስፋት ወደ ተግባራዊ የልማት ሥራ ወይንም ምርት ለመግባት ጥረት እየተደረገ ነው። በተመሳሳይ ሀብቱ ያላቸውና ወደ ምርት የገቡ ክልሎችን ተሞክሮ በመቀመር፣ በዘርፉ ለመሰማራት የሚፈልጉትንም ባለሀብቶች ለይቶና ከአካባቢው ወጣቶች ጋር በማስተሳሰር ወደ ሥራ ለመግባት ነው እየተሰራ ያለው። ደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ለኢንዱስትሪ ግብአት በስፋት የሚውል የብረት ማዕድን ባለቤትም ነው። በዚህ ረገድም ከዘርፉ ሙያተኞችና ባለድርሻ አካላት ጋር በስፋት በመነጋገርና በጥናትም የተደገፈ ሥራ በመሥራት ሀብቱ ጥቅም ላይ የሚውልበት አቅጣጫ ተዘርግቷል።

የክልሉ ማዕድን ሀብት በጥናትና ምርምር ተለይቶ ባለመታወቁና ከዚህ በፊትም በዘርፉ የተደራጀ መረጃ ባለመኖሩ ዘርፉ ላይ ቀጣይ የቤት ሥራ ይኖራል። ሀብቱ እንዲጠና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ለመሥራት በእንቅስቃሴ ላይ ይገኛል። በተለይም በአካባቢው ከሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር ለመሥራት በተለይም በየትምህርት ተቋማቱ ውስጥ የሚገኙ የጂኦሎጂ የትምህርት ክፍሎች እገዛ በማድረግ የሚኖራቸው ሚና ከፍተኛ በመሆኑ ግንኙነቱን ከነዚህ ክፍሎች ጋር በማጠናከር የተሻለ ሥራ ለመሥራት ታቅዷል።

**አዲስ ዘመን፡- ከደቡብ ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት ይከናወኑ ስለነበሩ ሥራዎች ምንም አይነት ሰነድ አልተገኘም? በማዕድን ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶችስ አልነበሩም?**

**ኢንጂነር ፍቅሬ፡-** የማዕድን ዘርፍ ሥራን በተመለከተ የተለዋወጥነውም ሰነድ የለም። በክልሉ በዘርፉ ላይ ስለሚገኙ ባለሀብቶች ጉዳይ በደንብ ግንዛቤ መያዝ ያለበት ነገር እስካሁን ባለው ሂደት ወርቅ የማምረት ሥራ በአካፋና በዶማ በመቆፈር በባህላዊ መንገድ ነው እየተከናወነ ያለው። ልማቱንም የሚያከናውኑት በማሕበር የተደራጁ የአካባቢው ነዋሪዎች ናቸው። ማዕድንን በዘመናዊ አሰራር ማልማት ብዙ ሥራ ይጠበቃል። አሁን ላይ በድንጋይ ከሰል ማዕድን ልማት ላይ ለመሰማራት በአንዳንድ ባለሀብቶች ጥያቄ እየቀረበ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የማእድን ሀብቱ በጥናትና ምርምር ገና እንዳልተለየ ቢገልፁልኝም ይሁን እንጂ በክልሉ እምቅ ሀብት እንዳለ ይታወቃል። ስለዚህ ጉዳይ ቢነግሩኝ?**

**ኢንጂነር ፍቅሬ፡-** ለጊዜው በስፋት የሚታወቁት የወርቅ፤ የድንጋይ ከሰልና የብረት ማዕድናት ናቸው።

**አዲስዘመን፡- ክልሉ ከተቋቋመ በአጭር ጊዜ ውስጥ የወርቅ ማዕድን ለማዕከላዊ ገበያ ማቅረቡ ይታወቃልና ይሄ በምን ሁኔታ ነው የተከናወነው?**

**ኢንጂነር ፍቅሬ፡-** ፍቃድ ያላቸው ወርቅ አዘዋዋሪዎች አሉ። እነዚህ አዘዋዋሪዎች በማሕበር ተደራጅተው በቁፋሮ ወይንም በባህላዊ መንገድ ከሚያለሙ በመግዛት ቀጥታ ለብሄራዊ ባንክ ያቀርባሉ።

**አዲስዘመን፡- ዘርፉን የሚመራው ማዕድንና ኢነርጂ ልማት ኤጀንሲ በምን ሁኔታ ነው ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ የሚያስተዳድረው ወይንም የሚመራው?**

**ኢንጂነር ፍቅሬ፡-** ተገቢ ጥያቄ ነው መዋቅሩ ላይ ብዙ ነገሮች መሰራት አለባቸው። ቅድሚያ ከሚሰጠው ሥራም አንዱ በክልሉ በየትኛው አካባቢ ምን አይነት ማዕድን፣ ምን ያህል ክምችት የሚለውን አውቆና ለይቶ መረጃ መያዝ ነው። ሥራውን የሚሰራ በሰው ኃይልም ተቋም ማጠናከርም ሌላው ተግባር ነው። ዘርፉ ለሥራ ዕድል ፈጠራም ያለው ሚና ከፍተኛ በመሆኑ ከዚህ አንጻር ጭምር ነው መቃኘት ያለበት። የተቋም አደረጃጀትም በክልል ደረጃ ኤጀንሲ አለ። በዞን ደረጃ ደግሞ የማዕድን ዘርፍ ጽህፈት ቤት ተቋቁሟል። በየደረጃው ደግሞ የወረዳ መዋቅር አለ። በዚህ መልኩ አንዱ ከሌላው ጋር በመናበብ ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ሥራዎች እየተሰሩ ነው።

**አዲስዘመን፡- የማዕድን ዘርፍ ብዙ የሰው ኃይል የሚይዝ መሆኑ ይታወቃል። ሥራውም የሚሰራው በማሕበር በመደራጀት በመሆኑ እስካሁን ባለው ሥራ ምን ያህሉቹ ተጠቃሚ ሆነዋል?**

**ኢንጂነር ፍቅሬ፡-** በዘርፉ ቁጥራቸው ከአስር በላይ የሆነ የተደራጁ ማሕበራት ይገኛሉ። ይሁን እንጂ ማሕበራቱ የተጠናከሩ ናቸው ለማለት አያስደፍርም። ድጋፍና ክትትል ያስፈልጋቸዋል። እኛም በትኩረት በዘርፉ ላይ ከምናደርገው እንቅስቃሴ አንዱ የማሕበራትን አቅም መገንባትና ተጠቃሚነታቸውን ከፍ ማድረግ ነው። በተለይም ሥራቸው በዘመናዊ አሰራር እንዲታገዝ ከማድረግ አንጻር እንዲሁም ልማት ያልተጀመረባቸውን አካባቢዎች ለይቶና አደራጅቶ ተጨማሪ የልማት ቦታዎችን በማመቻቸት የሥራ ዕድሉን በማስፋት የተጠቃሚዎችን ቁጥር መጨመር ነው። ከዘርፉ ባለሙያዎችና ከባለድርሻ አካላት ጋር ምክክሮችን በማድረግ ጠንካራ የማሕበር አደረጃጀቶች ለመፍጠር ነው የታቀደው።



ኢንጂነር ፍቅሬ ኃይሌ

**አዲስዘመን፡- ማዕድን ሚኒስቴር ዘርፉን ከሚመሩ የክልል ኃላፊዎች ጋር በቅርቡ የምክክር መድረክ ማካሄዱ ይታወሳልና በእናንተ በኩል ምን ይዛችሁ ተመለሳችሁ? ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጋር በቅርበት የምትሰሩበት ምቹ ሁኔታስ ተፈጥሯል?**

**ኢንጂነር ፍቅሬ፡-** ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ጋር የተካሄደው የምክክር መድረክ የአፈጻጸም ግምገማ ነው። በግምገማው አፈጻጸማቸው ጠንካራ የሆኑ ተጠናክረው እንዲቀጥሉ። ክፍተቶችና ደካማ የሆኑ አፈጻጸሞች ደግመው በቀጣይ ሥራ ታርመው እንዲሻሻሉ ነው። ትኩረት የተደረገባቸው የማድን ዘርፎች ደግሞ ለውጭ ገበያ ተልከው የውጭ ምንዛሪ በማስገኘት ድርሻ ባላቸው ላይ ነው። በተለይም ለአገር ኢኮኖሚ ዕድገት ከፍተኛ የሆነ ድርሻ ባለው በወርቅ ማዕድን ልማት ላይ በስፋት እንዲሰራ ትኩረት ተሰጥቷል። ሌላው በትኩረት እንዲሰራ በምክክሩ የተነሳው በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ከውጭ በግዥ ጥቅም ላይ እየዋለ ያለው የድንጋይ ከሰልን በአገር ውስጥ መተካት እንዲቻል ሥራዎች እንዲሰሩ ነው። ለማዳበሪያ ግብዓት በሚውሉ ማዕድናት ላይም በተመሳሳይ ትኩረት ተሰጥቷል። ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጋር ተቀራርቦ በመሥራት በኩል ለተነሳው ጥያቄ ሚኒስትሩን ጨምሮ በተለያየ የሥራ ኃላፊነት ላይ የሚገኙ በአንድ ወቅት ላይ ባህላዊ የወርቅ ልማት በሚካሄድባቸው አካባቢዎች ጉብኝት በማድረግ ያለውን ችግር አይተዋል። በተለይም ሚኒስትሩ ኢንጂነር ታከለ ኡማ ከክልሉ ጋር ለመሥራት ያላቸውን ፈቃደኝነት ገልጸዋል። ሀብቱ በሚገኝበት በክልሉ ዳውሮ ዞን ላይ ባለሀብቶች ለማልማት እንቅስቃሴ ጀምረዋል። ሚኒስትሩ አስፈላጊ በሆኑ ነገሮች ላይም ለክልሉ ድጋፍ እንደሚያደርጉ ቃል ገብተዋል።

**አዲስዘመን፡- ክልሉ የማዕድን ሀብቱን አልምቶ ለመጠቀም ያስፈልገኛል የሚለው ድጋፍ ምንድነው? ከማንስ ነው የሚጠብቀው?**

**ኢንጂነር ፍቅሬ፡-** ዘርፉን ለማልማት ሀብት እና የሰለጠነ የሰው ኃይል ይፈልጋል። የማዕድን ልማት የሚካሄድባቸው አካባቢዎች የመንገድ፣ የውሃ፣ የሙብራት በአጠቃላይ ከፍተኛ የሆነ የመሰረተልማት ችግር ያለባቸው ናቸው። ችግሮቹን ለመፍታት የተለያዩ አካላት ድጋፍ ያስፈልጋል። በዚህ ረገድም የፌዴራል መንግሥት ድጋፍ በእጅጉ ያስፈልጋል። የማዕድን ልማቱ ከባህላዊ አሰራር በማውጣት ልማቱን ለማሳደግ እውቀትና ልምድ ያላቸው የጥናት ባለሙያዎች ድጋፍም እንዲሁ ያስፈልጋል።

**አዲስዘመን፡- እንደተግዳሮት የሚያነሷቸው ነገሮች ካሉ ይግለጹልንና በዚሁ እናብቃ።**

**ኢንጂነር ፍቅሬ፡-** እንደ ተግዳሮት የማነሳው ሕገወጥ ዝውውር ነው። ውድ የሆነውና ለአገር ኢኮኖሚ ከፍተኛ ፋይዳ ያለው የወርቅ ማዕድን በሕገወጥ መንገድ ገበያ ላይ በማዋል የአገርን ጥቅም የሚያሳጡ አካላት ተግዳሮት ናቸው። ልማቱ በባህላዊ መንገድ መሰራቱም ከልማቱ ከሚገኘው ጥቅም ይልቅ የሚባክነው ይበዛል። የማዕድን ልማት በሚከናወንባቸው አካባቢዎች አልፎ አልፎ በሚያጋጥም የፀጥታ ችግር ልማቱ ይስተጓጎላል። ክልሉ ለነዚህ ማነቆዎች መፍትሄ ለመስጠት የራሱን ጥረት ያደርጋል።የማዕድን ዘርፉ በሰው ኃይል መጠናከር ይኖርበታል። የሥራ ቁሳቁስ ድጋፎችና ተሽከሪካሪ ድጋፍም ያስፈልጉታል። ማነቆዎቹን መፍታት ከተቻለ ኢኮኖሚን ሊያሻግር የሚችል የማዕድን ሀብት አለው።

**አዲስዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍላችን ስም አመሰግናለሁ!**

**ኢንጂነር ፍቅሬ፡-** እኔም አመሰግናለሁ!

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## ሰውነት መልካምነት

በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)

ወደ ክፍለ አገር እየሄድኩ አውቶቡስ ውስጥ ቁጭ ብያለሁ። በእድሜ ተዋረድ የተሳሉ አያሌ ነፍሶች ሸንጠ ረጅሙን አውቶቡስ ሞልተውታል። ካለፈለፈ የሚያመው የሚመስለው አንድ ወያላ ለግብገዛ በተመቸ ድምጽ ተሳፋሪ ይጣራል። ሀዋሳ...ሻሸመኔ እያለ። ጸጉሩን እየቆነደደ፣ እጁን በልብስ የተሸፈነ ገላው ውስጥ እያስገባ እያስወጣ፣ ወደዚያ ወደዚህ እየማተረ ይቁነጠነጣል። መኪናው ከሞላ ቆይቷል የት ላይ ሊጭን እንደሚጣራ ግራ ገብቶኝ በመስተዋቱ አሻግሬ አየዋለሁ። አፉ አያርፍም.. ሲያወራ ነው የማየው። አጠገቡ ካሉት ወዳጆቹ ጋር በአንድ ጊዜ ከሁሉም ጋር ይገባባል። ገረመኝ..ግን ለሀጢያት የበረታ ይመስለኛል። ሰው መቀመጫ አጥቶ በቆመበት አውቶቡስ ውስጥ ሌላ ተሳፋሪ መጥራቱ ማንነቱን እንድታዘብ አደረገኝ።

ከአውቶቡሱ የፊት በር አካባቢ ሹፌሩንና ረዳቱን ከበው የቆሙ አራት የሚሆኑ ወያላዎች ያንሾካሹካሉ። የሚሉትን ለመስማት ጓጉቼ ነበር.. አልተቻለኝም። በተቀመጥኩበት ግን እገምታለሁ..ግምት አንድ..ህገ ወጥ ስራ ሊሰሩ እያሴሩ መሰለኝ። ግምት ሁለት.. ትርፍ ለመጫንና ከታሪፍ በላይ ለማስከፈል እያደቡ መሰለኝ።

ግምት ሶስት.. እንዴት ብለው መንገድ ላይ የሚያስቆማቸውን ትራፊክ ማለፍ እንዳለባቸው እየመከሩም መሰለኝ። ከዚህ ሌላ ምን ሊሆን ይችላል? በሞላና መቀመጫ በታጣበት አውቶቡስ ውስጥ የነዛ ወያላዎች ተልዕኮ ሕዝብ ከማስጨነቅ ሌላ ምን ሊሆን ይችላል? እያልኩ አስባለሁ። ትኩረቴን ሳልነፍጋቸው በተቀመጥኩበት እከታተላቸው ጀመር። ለዚህ ምስኪን ተሳፋሪ ባህር የሚከፍሉ፣ እኚህን ፈርኦናውያን ወያላዎች ባህር የሚያሰምጥ አንድ ሙሴ መጥፋቱ አናደደኝ።

ያ ለፍላፊ ወያላ ወዲያ ወዲህ ተንጎራዶ ሁለት ተሳፋሪዎችን አግኝቶ ከቆሙት ጋር ቀላቀላቸው። የልቡ ደረሰ መሰለኝ እንደ እሱ የከፋት ሀሳብ ካነገበ የአውቶቡሱ ረዳት ጋር ሂሳብ መክፈያ ደረሰኝ ይዘው ትኬት መቁረጥ ጀመሩ። በዚያ ሰዓት ከረዳቱና ከዛ ለፍላፊ ወያላ ፊት በቀር የሁሉም ተሳፋሪ ፊት ሀዘን አጥልቶበት ነበር።

ከተሳፋሪዎቹ ወደ ረዳቱ የሚወናጨፉ የማይሰሙ አንዳንድ ጉርምርምታዎች ይሰሙኛል። በታሪፍ ይሆናል ስል አሰብኩ... እንዳሰብኩትም አልቀረም ያ ሁሉ ድምጽ አልባ ጉርምርምታ በረዳቱ ያልተገባ የታሪፍ ጭማሪ ነበር። መንግስት የሚያውቀው ታሪፍ መቶ ሰላሳ አምስት ብር ሆኖ ሳለ ያ ረዳት ግን ሁለት መቶ ሀምሳ ብር ነበር ሲያስከፍል የነበረው። ተናደድኩ... እውነት ተናደድኩ... ለዚህ ድሀ ሕዝብ ሙሴን መሆን አለመቻሌ ራሴን እንድታዘበው አደረገኝ።

አገራችን ሰው ነው ያጣችው... ልክ እንዲህ እንደ አሁኑ ክፉ ነገርን የሚቃወም ሰው። እያዩ ዝም ማለት ወንጀልን ከማስፋፋት ባለፈ አገርን በእጅጉ የሚጎዳ ድርጊት እንደሆነ የገባኝ ሁለት መቶ ሃምሳ ብር መክፈል አቅቷቸው የሚያለቅሱ ድሆችን ሳይ ነበር። ውስጤ የሆነ የእልህ ስሜት ተፈጠረ..። የነዛን ድሆች እንባ አይቶ ዝም የማይልና፣ የነዛን ራስ ወዳድ ረዳትና ወያላ ተግባር የማይታገስ እልህ።

በዚህ መሀል ቆብ የደፋ አንድ መነኩሴ በሚያሳዝን ድምጽ ወደ ረዳቱ እያዩ ‹ልጄ እኔ ዘዋይ ነው የምወርደው፣ 250 ብር የለኝም... እባክህ ግማሹን ልክፈልህ› ብለው ሲማጸኑት ሰማሁ።

እንዴት እንዳመናጨቃቸው... እናት እንደዛ ስትመናጨቅ፣ መነኩሴ እንደዛ ሲገፉ ያን ቀን ነው ያየሁት። ‹ከፈለጉ ይውረዱ... ሌላ ሰው እጭናለሁ› አለ። በዚህ መሀል አንድ ሞገደኛ ድምጽ ተሰማ ‹አንተ ለምን በሥርዓት አታናግራቸውም? ወንጀል መስራትህ ሳያንስ ትልቅ ሰው ታመናጭቃለህ እንዴ? ይቺን ተናግሮ መናኸሪያ ግቢ ውስጥ ወዳለው የትራንስፖርት ስምሪት ክፍል በመሄድ ስለተፈጠረው ነገር ሁሉ ተናገረ።

‹ማህበረሰቡን በታማኝነት የማገልገል ግዴታችሁን እየተወጣችሁ አይደለም። ማንም ባልተገባ ታሪፍ ተሳፋሪን ሲበዘብዝ ዝምታን መርጣችኋል። የተጠያቂነት ሀላፊነታችሁን አልተወጣችሁም። እናንተ የምትመሩት ማህበር የሙያ ስነምግባር የላችሁም› ሲል ለሚመለከተው አካል አቤቱታውን አቀረበ። ይሄን የሰማው ስራ አስኪያጅ አጠገቡ ያለውን ድምጽ ማጉያ በማንሳት የመኪናውን ታርጋ ቁጥር በመጥቀስ ከመናኸሪያ ግቢ እንዳይወጣ ለጥበቃዎች ትዕዛዝ አስተላለፈ። ያ መኪና ከመቀጣትም አልፎ መንግስት በሚያውቀው ነባር ታሪፍ እንዲጭን ተገደደ።

በዛ ልጅ ሙሴነት አርነት ወጣን። በዛ ልጅ ሙሴነት ባህር ተሻገርን። ያ ልጅ የነዛ ድሀ ነፍሶች እንባና የነዛ ራስ ወዳድ ረዳትና ወያላ እኩይ ስራ የነቀነቀው ባላደራ ነፍስ ነበር... ያም ልጅ እኔ ነበርኩ። ጭቁኖችን እንደመርዳት፣ ድምጽ ለሌላቸው ድምጽ እንደመሆን በዚህ ዓለም ላይ ምን ደስታ አለ? ሰውነት ቢለካ፣ ማስተዋል ቢመዘን ማረፊያው አገርና ሕዝብ ይሆኑ ነበር ስል እያሰብኩ በጀግንነት ወደ ቦታዬ ተመለስኩ። ወደ መኪናው ስገባ ከረዳቱና ከወያላው ፊት በቀር የሁሉም ተሳፋሪ ፊት ደስታ ነግሶበት ነበር። ደስ አለኝ... ለዛ ሁሉ ተበዳይ ሳቅ በመሆኔ።

ከተቀመጥኩበት ሰዓት መኪናው እስኪንቀሳቀስ ድረስ ስለዝምታና ጩኸት እያሰብኩ ነበር። ዝዋይ ደርሰን ለምሳ እስከወረድንበትና እኚያ መነኩሴ በስራዬ ተደስተው እግዚአብሔር ይባርክህ እስካሉኝ ጊዜ ድረስ ስለ ሰውነት እያሰብኩ ነበር። ሁሉም ነገር ያለቦታው ስህተት ነው። ቦታው እየመሰለን በብዙ ነገር ላይ ስህተት ሰርተናል። ለካ ዝምታ መብትንና ሀላፊነትን አሳልፎ መስጠት ነው። ለካ ዝምታ መሸነፍ ነው። ለካ ካለመናገር ደጀዝማችነት ይቀራል። ለካ ዝምታ ሳይሆን መናገር ነው ወርቅ እያልኩ። ሰው በወጉ ማሰብ ካልቻለ የጫካ እንስሳ ነው። ሰው ተፈጥሮውን ካልተረዳ የአጋንት ባሪያ ነው። ሰው በሀሳቡና በተግባሩ በጎነት ከሌለው አውሬ ነው። አምላክ በሀጢአታችን አዝኖ ከነፍሳችን እስከራቀበት ጊዜ ድረስ የሰው ልጅ እንደ እግዚአብሔር ነበር እያልኩ።

እስከዛሬ ድረስ እንደ አገርም ሆነ እንደ ዜጋ የተጎዳንባቸው ነገሮች ሳንናገር ዝም ያልንባቸው እንደሆኑ ዛሬ ነው የገባኝ። ሕዝባችን እውነት ጠፍቶታል፣ እውነትና ውሸት ተደበላልቆበታል። ሰው በጠራራ ጸሀይ ሲዘረፍ እያየን እኔ ላይ ካልደረሰ በሚል ዝም የምንል አራዳ መሳይ ፋራዎች ብዙ ነን። የሌሎች መብት ሲነካ እያየንና እየሰማን በእኛ ላይ ካልደረሰ ብለን የማንናገር አለን። አገር ማለት በእኔና በሌላው ሰው የያገባኛል ስሜት የምትጸና እንደሆነች የገባን ጥቂቶች ነን። ሌሎች በሚለፉባትና ሌሎች በሚደከሙባት አገር ላይ በነጻነት እየኖርኩ እንደሆነ ሳስብ እንደ ዜጋ ለአገሬ አንዳች ባለማዋጣቴ ሀፍረት ተሰማኝ። ከዚህ በኋላ ባለው ሕይወቴ ለአገሬና ለሕዝቤ ሙሴን ለመሆን እያሰብኩ ሀዋሳ ደረስኩ።

# ዓለም አቀፍ

## የእንግሊዝ ትልልቅ ሬስቶራንቶች ምግቦቻቸው የያዙትን ካሎሪ ይፋ ማድረግ ሊጀምሩ ነው

በጋዜጣው ሪፖርተር



እንግሊዝ ውስጥ ከትናንት ጀምሮ ወደ ምግብ ቤት የሚያቀኑ ሰዎች በሜኑ ወይም የምግብ እና የዋጋ ዝርዝር ማቅረቢያ ላይ እያንዳንዱ ምግብ ያለውን ካሎሪ ማግኘት ይችላሉ።

በመሆኑም ከ250 በላይ ሠራተኞች ያሏቸው ምግብ ቤቶችና ካፍቴሪያዎች የሚያዘጋጇቸው ምግቦች ውስጥ ምን ያህል ካሎሪ እንዳለ በሜኑዎቻቸውና በድረ ገጻቸው ላይ ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል።

አዲሱ ሕግ ሰዎች ጤናማ ምርጫ በማድረግ ከመጠን ያለፈ ውፍረትን ለመቋቋም መንግሥት ያወጣው ዕቅድ አካል ነው።

አንዳንድ ምግብ ቤቶች ሕጉ ወጪያችንን ይጨምራል ብለው ሰግተዋል። በአመጋገብ ችግር ላይ የሚሠራ የበጎ አድራጎት ድርጅት ደግሞ ሕጉ ለጎጂ አስተሳሰቦች እና ባህሪያት አስተዋፅኦ ይኖረዋል ብሏል።

በአዲሱ ሕግ መሠረት በእንግሊዝ የሚገኙ 250 እና ከዚያ በላይ ሠራተኞች ያሏቸው የምግብ እና የመጠጥ ቤቶች ቀድመው ካልተዘጋጁ ምግቦች እና ለስላሳ መጠጦች ውጭ የካሎሪ መረጃ ማሳየት አለባቸው።

እንደ ዌዘርስፑንስ ፐብስ እና የሪል ግሪክ ሬስቶራንት ያሉት ስለሚያበስሉት ምግብ የካሎሪ ይዘት መረጃ በሜኑዋቸው ላይ ያትማሉ። ማክዶናልድም ይህን ማድረግ ከጀመረ ከአስር ዓመታት በላይ ሆኖታል።

የሜክሲኮ ምግብ በማሰናዳት ስም ያተረፈው የዋሃካ መስራች ማርክ ሴልቢ ለቢቢሲ እንደተናገሩት ድርጅቱ ለደንበኞቹ በሚያቀርበው ምግብ እና መጠጥ መረጃ ላይ "ግልጽ ለመሆን ዝግጁ ነው" ብለዋል። ካሎሪንን በመለካት ላይ ያለው ትኩረት ችግር መሆኑንም ጠቁመዋል።

"ይህ የታሪኩን አንድ ክፍል ብቻ ይነግረናል። የበለጠ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል ብለን የምናስበውን በምግብ ዙሪያ አንዳንድ በጣም አስፈላጊ የሆኑ መሰረታዊ ነገሮችን ግን ይዘነጋል። ይህም በእርግጠኝነት ሊታሰብበት የሚገባ ይመስለኛል።" ብለዋል።

ሰዎች ዋሃካን የሚጎበኙት እንደ "ግብዣ" መሆኑን እንደሚያምኑ ሴልቢ ገልጸው ማንም ሜኑውን ከካሎሪ አንጻር እንደማይመለከተው ተናግረዋል።

በተጨማሪም ምግብ አብሳዮች በምግብ ቤቶች ውስጥ በየቀኑ የሚጠቀሙባቸውን 250 ግብአቶች በትክክል መጠቀማቸውን የሚያረጋግጥ አሠራር መፍጠር በንግዱ ላይ "በግልጽ ተጽእኖ በማሳደር ወጪውን ያንራል" ብለዋል።

ኩባንያው ለውጡን በመጠቀም እያንዳንዱ ምግብ የአየር ንብረት ላይ ያለውን ተፅዕኖ ለመለካት ተጠቅሞበታል ብሏል።

የማስተር ሼፍ ውድድር ወይም የምግብ አብሳዮች ውድድር አሸናፊው ስቬን-ሃንሰን ብሪት በትዊተር ገፃቸው ለውጡ "በኢንዱስትሪው ላይ የደረሰ አሰቃቂ ነገር ነው" ብሏል። ሕጉ "ፈጠራን፣ ልዩ መሆንን የሚያቆም እና ወደ አሰልቺ ምግብ የማብሰል አሠራር ሊያመራ ይችላል" ሲልም አስጠንቅቋል።

"ልጆች የሚያድጉት በሬስቶራንቶች፣ በሆቴሎች እና በካፌዎች ውስጥ ከምግቡ ስር ያለውን ትንሽ ቁጥር ብቻ በመመልከት ነው። ምርጫ የሚደረገው በቁጥር ላይ ተመርኩዞ ብቻ ነው። ጣዕም፣ ግብዓት፣ ታሪክ፣ የምግብ አሰራር ወይም የተመጣጠነ ምግብ ተፈላጊነት ይጠፋ እና ይሸፈናል። ትኩረቱም ወደ አዲስ አቅጣጫ ይዞራል" ብሏል።

የዩኬ ሆስፒታሊቲ ኃላፊ ኬት ኒኮልስ አዲሱ ሕግ "ሥራቸውን ለማስቀጠል ለሚታገሉት በሺህዎች የሚቆጠሩ ድርጅቶች በጣም በመጥፎ ጊዜ የመጣ ነው" ብለዋል።

"የካሎሪ መጠን ማሳወቂያ አተገባበር እንዲዘገይ ከረዥም ጊዜ ጀምሮ ጠይቀን ነበር። ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ አስገዳጅ እንዳይሆን እና የተወሰነ የማስተንፈሻ ጊዜ ያስፈልጋል" ሲሉም አክለዋል።

"በኮቪድ ምክንያት ባለፉት 24 ወራት የተንገዳገዱ ድርጅቶች ኪሳራቸውን እንዲመልሱ የሚጠበቁ ንግዶች ውስብስብ እና ውድ የሆኑ አዲስ መረጃ በድንገት እንዲያስተዋውቁ መጠበቅ በጣም አሳሳቢ ነው።" ብለዋል ኬት ኒኮልስ ቻርሎት ሮበርትስ ለተባለችው የማክልስ ፊልድ ነዋሪ ለውጡ በምግብ ምርጫዋ ላይ ምንም ተጽዕኖ አይኖረውም።

"ወደ ሬስቶራንቱ የመጣሁት መብላት የምፈልገውን አውቄ ነው። ጥሩ ምግብ እንደሚሆን እያወቅኩ ወደዚያ እሄዳለሁ። መብላት የምፈልገውን ብቻ ነው የምበላው" ትላለች የ19 ዓመቷ ወጣት።

የለንደን ነዋሪው ጄምስ ሃውለትም ለውጡ በምርጫው ላይ ተጽዕኖ እንደማይኖረው ተናግሯል። "መረጃዎቹን እንዳለ ሰፈሩ አላስተዋልኩም ነበር" ብሏል።

"በየትኛውም ቀን የሚሰማኝ ነው የሚሆነው። ፒዛ ከፈለግኩ ፒዛ እመገባለሁ። በርገር ካማረኝም በርገር አዛለሁ።"

ከሞንማውዝ ለመጡት የ57 ዓመቱ ፓትሪክ ካላጋን ግን እርምጃው በምግብ ምርጫቸው ላይ ለውጥ እንደሚያመጣ ይናገራሉ።

"ሰዎች ለሚመገቡት ነገር ትኩረት ይሰጣሉ ብዬ አስባለሁ። ከኮሮና ወረርሽኝ በኋላ ሰዎች የበለጠ ንቁ የሆኑ ሲሆን ስለሚወስዱት ካሎሪም የማወቅ ፍላጎት አላቸው" ሲሉ ለቢቢሲ ተናግረዋል።

የ56 ዓመቷ ኬት ካላጋን ሰዎች "ለምንበላው ነገር ራሳችን ኃላፊነት መውሰድ አለብን" ሲሉ በሕጉ መስማማታቸውን አስታውቀዋል።

በዩናይትድ ኪንግደም የአመጋገብ ሥርዓት ችግር ላይ የሚሠራው ቢት የተሰኘው በጎ አድራጎት ድርጅት እንደሚለው በምግብ ዝርዝር ውስጥ ካሎሪ መጥቀስ አስገዳጅ መደረጉ ለጎጂ የአመጋገብ ችግር አስተሳሰቦች እና ባህሪያት መባባስ አስተዋጽኦ ያደርጋል።

የበጎ አድራጎት ድርጅቱ የውጭ ጉዳይ ዳይሬክተር ቶም ኩዊን እንዳሉት የካሎሪ መረጃ በአመጋገብ ችግር የተጎዱ ሰዎች ላይ ጭንቀትና ድብርት እንደሚፈጥር የሚያሳይ ማስረጃ አለ።

"ሕጉ የሰዎችን የአመጋገብ ልማዶችን ስለመቀየሩ የሚያሳዩ ማስረጃዎች በጣም ውስን ናቸው" ብለዋል።

ቢት ለቢቢሲ እንደገለጸው በእንግሊዝ ብቻ 1.25 ሚሊዮን ሰዎች የአመጋገብ ችግር አለባቸው። መንግሥት በአመጋገብ ችግር በተጎዱ ሰዎች ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ እንዲያሰላስል እና "የአመጋገብ ችግር ባለሙያዎችን እንዲያማክር" ያለማቋረጥ መጠየቁን አስታውቋል።

ከመጠን ያለፈ ውፍረት አገሪቱ ካጋጠሟት የጤና ችግሮች አንዱ መሆኑን የጤና እና የማኅበራዊ እንክብካቤ ሚኒስቴር አስታውቋል። የምግብ ዝርዝር መገለጹ ሰዎች ጤናማ ምርጫ እንዲያደርጉ በመረዳት ረገድ ትልቅ ሚና እንዳለው ተናግሯል።

የሚኒስቴሩ ቃል አቀባይ አክለውም ሰዎች በሱፐር ማርኬቶች የሚሸጡ ምርቶችን የምግብ መረጃ ማየትን ተለማምደዋል ብለዋል።

መንግሥት ፖሊሲው በጥናት የተረጋገጠ መሆኑን አስታውቋል። ከአዕምሮ ጤና በጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ባለሙያዎች ጋር "በሰፊው" መምከሩንም ገልጿል።

# ስፖርት





# ክለቡ ውጤታማ አትሌቶቹን ሸለመ

**ብርሃን ፈይሳ**

በ2002 ዓ.ም የስፖርቱን መቀዛቀዝ ተከትሎ የወቅቱ የኦሮሚያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አነሳሽነት ‹‹ኦሮሚያን የአትሌቶች ምንጭ ብቻ ሳይሆን ጎርፍም እናደርጋታለን›› በሚል መርህ በርካታ ክለቦች እንዲቋቋሙ መደረጉ የሚታወስ ነው። በወቅቱ ከተመሰረቱ 20 ክለቦች መካከል እስካሁን በሥራ ላይ ያሉት ከአምስት ያልበለጡ ሲሆኑ፤ የኦሮሚያ ደን እና ዱር እንስሳት ድርጅት የአትሌቲክስ ስፖርት ክለብ አንዱ ነው። ድርጅቱ በአሁኑ ወቅት በሁለቱም ጾታ 46 አትሌቶችን በማቀፍ እንደ ሳሙኤል ተፈራ፣ ጭምዴሳ ደበሌ፣ ትዕግስት ከተማን የመሳሰሉ ታዋቂ አትሌቶችን በማፍራት ላይ ይገኛል።

የኦሮሚያ ደን እና የዱር እንስሳት ድርጅት ከሚያበረክታቸው የማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎቶች መካከል አንዱ የአትሌቲክስ ክለብን ማቋቋሙና በስፖርቱ ዘርፍ ውጤታማ መሆኑ ነው። ክለቡ በዚህ ዓመት ብቻ በተካሄዱ የተለያዩ አገር አቀፍ የአትሌቲክስ ቻምፒዮና ተሳትፎዎቹ 8የወርቅ፣ 8የብር፣ 9የነሃስ ሜዳሊያዎችን እንዲሁም 10 ዲፕሎማዎችን አስመዝግቧል። በቶኪዮ ኦሊምፒክ ኢትዮጵያን ለሚወክለው ብሄራዊ ቡድን ሰባት የሚሆኑ አትሌቶች በእጩነት ቀርበውም ነበር። ክለቡ ከመሃል ከተማ ወጣ በማለት የአየር ሁኔታውና የቦታ አቀማመጡ ለስፖርቱ በእጅጉ ጠቃሚ በሆነው እንጦጦ ካምፕ አስገንብቷል። ይኸውም አትሌቶቹ በስፖርቱ ለውጤታማነት እንዲያተጉ ምክንያት በመሆኑ ያስመሰግነዋል።

ኢትዮጵያ ከምትታወቅባቸው የአትሌቲክስ ውድድር ርቀቶች መካከል በ1ሺ500ሜትር አስደናቂ አቋማቸውን እያሳዩ ካሉ ወጣቶች መካከል አንዱ ሳሙኤል ተፈራ ነው። እ.አ.አ 2018 በዓለም የቤት ውስጥ አትሌቲክስ ቻምፒዮና ሳይታሰብ የወርቅ ሜዳሊያ ያጠለቀው አትሌቱ ጉዳት በማስተናገዱ ምክንያት ከውድድር ርቆ ቆይቷል። ከጉዳቱ አገግሞ በቶኪዮ ኦሊምፒክ ተሳታፊ ቢሆንም ውጤታማ ለመሆን ግን አልቻለም። በመጨረሻም በኦሊምፒክ ማግስት በተካፈለበት የዓለም የቤት ውስጥ ቻምፒዮናም በድጋሚ ቻምፒዮን በመሆን አድናቆትን አግኝቷል።

በ18ኛው የዓለም የቤት ውስጥ ቻምፒዮና 4 የወርቅ፣ 3 የብር እና 2 የነሃስ በጥቅሉ 9 ሜዳሊያዎችን በማግኘት ከዓለም በቀዳሚነት ውድድሩን ማጠናቀቁ የሚታወስ ነው። በዚህ ውድድር የመጨረሻውን የወርቅ ሜዳሊያ በእጁ በማስገባት ሃገሩን ከዓለም አንደኛ በማድረግም የስፖርት ቤተሰቡን አኩርቷል። ይህንን ተከትሎም ክለቡ የኦሮሚያ ደን እና ዱር እንስሳት ድርጅት የሽልማት መርሐ ግብር አዘጋጅቷል። ክለቡ ለአሰልጣኞች እና ሁሉ በዓለም አቀፍ ውድድር ውጤታማ ለሆነው ሌላኛው አትሌት ጭምዴሳ ደበሌ የገንዘብ ሽልማት አበርክቷል።

የኦሮሚያ ደንና ዱር እንስሳት ድርጅት ሥራ አስኪያጅ አቶ አራርሳ ረጋሳ ይጠቁማሉ። በእውቅና መርሐ ግብሩን በሁለት ምክንያቶች የተዘጋጀ ሲሆን፤ ከክለቡ አልፎ የሃገሩን ስም ለማስጠራት የበቃው አትሌት ሳሙኤል ተፈራን ማመስገን ቀዳሚው ነው። ሌላው ደግሞ በክለቡ የታቀፉ አትሌቶችም ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያግዛቸው መሆኑን ጠቁመዋል። በመሆኑም አትሌቶቹ ውጤታማ በመሆን የሃገራቸውን ስምና ሰንደቅ ለማስጠራት መትጋት እንደሚገባቸው አመላክተዋል።

ለሁለተኛ ጊዜ የቤት ውስጥ ውድድር ቻምፒዮን ለመሆን የቻለውና ከጉዳት መልስ ብቃቱን ያስመሰከረው ወጣቱ አትሌት ሳሙኤል፤ ድርጅቱ የእውቅና መርሐ ግብር በማዘጋጀቱ ምስጋናውን አቅርቧል። ሽልማቱ ለተቀሩት አትሌቶች ትልቅ መነሳሳትን የሚፈጥር ሲሆን፤ በቀጣይም ከሞራል ጀምሮ የሚደረገው ድጋፍ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪ አቅርቧል።

መካከለኛና ረጅም ርቀት አሰልጣኝ ብርሃኑ መኮንን በበኩላቸው፤ ድርጅቱ ለአትሌቶች ምሳሌ የሚሆነውን የሽልማት መርሐ ግብር በማዘጋጀቱ አመስግነዋል። ክለብ ከማቋቋም ባለፈ ካምፕ በመክፈትም ጭምር እስከ አሁን ድረስ መቆየቱም ያስመሰግነዋል። ክለባቸው ከ14 ዓመት ጀምሮ ያሉ ታዳጊዎችን በተለያዩ ስፍራዎች በመገኘት መልምሎ ወደ ክለቡ ይቀላቅላል። እስካሁንም በርካታ




ተተኪ አትሌቶችን በማፍራት ለሌሎች ክለቦችም ጭምር ግብዓት ለመሆን ችሏል።

ይሁንና ክለቡ ቀድሞ በነበረበት ሁኔታ አንጻር መቀዛቀዝ ይስተዋልበት ነበር፤ ይኸውም ከዚህ ቀደም ካምፑ ባለበት ስፍራ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ይገነባል ቢባልም እስካሁን ተግባራዊ አልሆነም። በመሆኑም ለወደፊት አሁን የተፈጠረውን መነሳሳት ተከትሎ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ይሟላሉ የሚል ተስፋውን አንጸባርቋል። ከዚህ ባለፈ እንደ ሃገር ክለቦችን አቋቁመው ያፈረሱትን ተጠያቂ ማድረግ እንዲሁም እስካሁን የቀጠሉትን ደግሞ ማበረታታት የሚቻልበት አሰራር ሊፈጠር እንደሚገባም አሰልጣኙ ጠቁሟል።


# የጨረታ ማስታወቂያ

**በስሚ ኩራ ክ/ከተማ አስተዳደር የአራብሳ 1ኛ ደ/ት/ቤት ፋይናንስ ግዢ**

የአራብሳ 1ኛ ደ/ት/ቤት ለ2014 ዓ.ም የሁለተኛ ዙር ጨረታ ለማውጣት (02) በጀት ዓመት የሚያገለግሉ 1. የደንብ ልብስ፣ 2. የፅህፈት እቃዎች፣ 3. የፅዳት እቃዎች፣ 4. ለህንፃ መሳሪያዎች፣ 5. የጥገና ስራዎች፣ 6. ቋሚ እቃዎች፣ 7. ልዩ ልዩ እቃዎች፣ 8. የስልጠና ተጫራቾች የሚከተሉትን የጨረታ መመሪያ ነጥቦች በመረዳት በጨረታ ሰነድ ላይ መግለጽ ይኖርባቸዋል።

1. ተጫራቾች በዘርፉ የተሰማሩበትን ሕጋዊ ንግድ ፈቃድ ያላቸውን የዘመኑን ግብር ስለመክፈላቸው ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ።
2. በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በአቅራቢነት የተመዘገበና ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ።
3. የ2014 ዓ.ም የታደሰ የንግድ ፍቃድ ያላቸው።
4. በተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ከሆነ ከዚህ በታች የተጠቀሰውን የጨረታ ማስከበሪያ የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ።
5. ተጫራቾች ከዚህ በታች የተጠቀሰውን የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ የተረጋገጠ በየሎቱ ፊት ለፊት የተቀመጠው ገንዘብ ሲፒኦ CPO ማስያዝ ይኖርባቸዋል።

| ሉት ቁጥር | የሉት ዝርዝር ንብረት አስተዳደር የስራ ሂደት | የተጠየቀው የጨረታ ማስከበሪያ በኢትዮ. ብር |
|---|---|---|
| ሎት 1 | የደንብ ልብስ | 6,000 |
| ሎት 2 | የፅህፈት እቃዎች | 2,000 |
| ሎት 3 | የፅዳት እቃዎች | 1,000 |
| ሎት 4 | ለህንፃ መሳሪያዎች | 2,000 |
| ሎት 5 | የጥገና ስራዎች | 10,000 |
| ሎት 6 | ቋሚ እቃዎች | 7,000 |
| ሎት 7 | ልዩ ልዩ እቃዎች | 1,000 |
| ሎት 8 | የስልጠና | 1,000 |

6. የጨረታ ሰነዱን ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በየሎቱ የማይመለስ ብር 100.00 (አንድ መቶ ብር) በመክፈል የተዘጋጀውን ሰነድ ከት/ቤቱ ቢሮ ቁጥር 93 እየቀረቡ መግዛት ይችላሉ። በጥቃቅንና አነስተኛ ምርት ብቻ ከክፍያ ነፃ ካደራጃቸው አካል ደብዳቤ በመፃፍ እና ለሚያመርቱት ምርት (ዕቃ) እንደማንኛውም ተጫራች ሰነድ በመግዛት ጨረታውን መሳተፍ ይችላሉ።
7. ተጫራቾች ማስታወቂያው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ 10 ተከታታይ የስራ ቀናት ቢሮ ቁጥር 93 ድረስ በመምጣት ዋጋው የተሞላበትን የጨረታ ሰነዱን ዋናውን እና ፎቶ ኮፒውን ለየብቻው በማሸግ ለዚህ በተዘጋጀው የጨረታ ሣጥን ውስጥ ማስገባት አለባቸው።
8. ጨረታው በጋዜጣ ከወጣበት በ10ኛው ቀን 10፡30 ሰዓት ተዘግቶ 11ኛው ቀን 4፡00 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል። የጨረታው መዝጊያና መክፈቻ የስራ ቀን ካልሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን በተመሳሳይ ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል።
9. ተጫራቾች አሸናፊነታቸው እንደተገለፀላቸው የውል ማስከበሪያ 10 ፐርሰንት ሲፒኦ ዋስትና ማስያዝ አለባቸው።
10. ተጫራቾች ጨረታው ከመከፈቱ በፊት ለሚወዳደሩበት ናሙና ለሚቀርብባቸው እቃ ናሙና ማቅረብ አለባቸው። ናሙና የማይቀርብባቸው ቋሚ እቃዎች መስሪያ ቤቱ ባቀረበው ስፔስፊኬሽን መሰረት ማቅረብ አለባቸው።
11. በጨረታው አሸናፊ የሆኑ ድርጅቶች በራሳቸው ትራንስፖርት በማጓጓዝ መስሪያ ቤቱን ንብረት ክፍል ድረስ በማስገባት ማስረከብ ይኖርባቸዋል።
12. ተጫራቾች ባሸነፉት እቃዎች ላይ መስሪያ ቤቱ 20 ፐርሰንት መቀነስ 20 ፐርሰንት የመጨመር መብቱ የተጠበቀ ነው።
13. በጨረታው አሸናፊ የሆኑ ድርጅቶች እቃ ሙሉ በሙሉ በጥራት ካለፈ በኋላ ንብረት ክፍል ከገባ ብር ይከፍላል።

## በስሚ ኩራ ክ/ከተማ ወረዳ 04

## አራብሳ አፀደ ህፃናትና የመ/ደ/ት/ቤት